


እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ



# ትንሣኤ



ቁጥር ፳፬ ሚያዝያ ፲፱፻፸፰ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፣

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፣


# ማ ው ጫ

አርእስት ፣ ገጽ


ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእሰ አንቀጽ ........ ፪
ዳግም ምጽአት ........ ፭
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፮
ጾም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ሥርዓት ........ ፯
ዜና ሊቃውንት ........ ፱
ታላቁ ያዕቆብ ........ ፲፩
ከመንበር ወደ መስቀል ........ ፲፪
የአቶ ሙላቱ ኩች ዜና ዕረፍትና አጭር የሕይወት ታሪክ ........ ፲፭
የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ ........ ፲፮
ከመስማት ጋር ማየት ........ ፲፰
በኩረ ትንሣኤ ........ ፲፱
ቅዱሳት አንስት ........ ፳፩
ከደብረ ዘይት እስከ ሆሣዕና ........ ፳፪
ትምህርተ ግዕዝ ........ ፳፬


## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በእግዚአብሔር ስም እንደምን አላችሁ የሚለውን መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከሰላምታየ ቀጥየ የሚከተለውን መልዕክት በመጽሔት ላይ አውጥታችሁ ላየሁትና ስሕተት መስሎ ሊታየኝ ከትምህርት ጋር ማሳሰቢያ እንደምትሠጡልኝ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ ።

ይኸውም በናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ያየሁት ተገቢ ያልሆነ ነገር ነው ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ናዝሬት ሄጄ ስለነበር በዕለተ ሰንበት ከቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ሄጄ ስጸልይ ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ልኡካኑ ቅዳሴ ገቡ እኔና ለማስቀደስ መለድ ብሎ የመጣው ሕዝበ ክርስቲያን ጸሎተ ቅዳሴውን ስንሳተፍ ሳለን ጸሎተ ቅዳሴው ገና ሳይጋመስ በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ኃይለኛ ድምፅ ያለው ላውድ እስፒከር (ድምፅ ማጉሊያ) ይዘው የዚያው ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን ናቸው ትምህርት ጀመሩና ትንሽ እንዳስተማሩ ገንዘብ ልመና ጀመሩ አንድ ምዕመን ገና ከግቢው ሲገቡ አቶ እገሌ መጣህ ! እግዚአብሔር ያምጣህ! በል ወደዚህ ናና መጀመሪያ ከዚህች መሶበ ወርቅ ላይ እስኪጣልባት እያሉ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሳይሳለም እንኳ ገንዘብ አምጣ እያሉ ሲያስገድዱ ተመለከትሁ ያንን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም አምጡ ስጡ በማለት ይጮሃሉ ፣ የውጭም የግቢውም ሕዝበ ክርስቲያን በዚሁ ጩኸት ስለሚደናቆር የቅዳሴውን ጸሎት ለመከታተል ሳይችል ቅዳሴው አበቃ በቅዳሴ ጊዜ የዚህ ዓይነት አድራጐት እንዲፈጸም የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ ያዝዛል?

ቢለመንስ በቅዳሴ ላይ ነው የሚለመነው እንዴት! ቅዳሴው የሚቀደሰው ለሕዝበ ክርስቲያኑ ነው ? ወይስ ለእምስቱ ልዑካን ? ከጩኸቱ የተነሣ አንድ ነገር ሳልሰማ ከቤተ ክርስቲያን ተመለስኩኝ ስለዚህ ትምህርት እንድትሰጡበት በትሕትና አሳስባለሁ ።

ከምዕመናን አንዱ

ጠያቂው የተጸውዖ ስመዎን አለመግለጽዎ ትክክል አይደለም ማንኛውም ጠያቂ ስሙን የመግለጽ ግዴታ አለበት ወደፊት በጥያቄው መጨረሻ ስሙን ለማይጽፍ ሰው ለጥያቄው መልስ አይሰጠውም ።

ነገር ግን ይህ ጥያቄ መልስ ሊሰጥበት የሚገባ ስለሆነ መልሱን ቀጥለን አቅርበነዋል ።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሮ እስከሚፈጸም ድረስ ከዚያው ከጸሎተ ቅዳሴው በስተቀር ሌላ የግል ጸሎት መጸለይ መናገር ሌላ የተለየ ሥራ መሥራት ወዲያና ወዲህ ማለት ከሥነ ሥርዓት ውጭ ነው ።

በቅዳሴ ጊዜ የተቻለው መቋሚያ ሳይዝ ድጋፍ ሳይፈልግ ተሰጥዎ ከመቀበል በስተቀር ሌላ ነገር ሳይናገር ፣ ቁሞ ለማስቀደስ የማይችል ከሆነ ደግሞ መቋሚያ ይዞ ፣ ድጋፍ ተደግፎ ፣ ካልቻለም ተቀምጦ የጸሎተ ቅዳሴው ተካፋይ የመሆን ግዴታ አለበት ።

ጸሎተ ቅዳሴው እስከሚፈጸም ድረስ ለመቆየት የማይችል ከሆነ ግን ቅዳሴው ከመጀመሩ አስቀድሞ መውጣት እንዳለበት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያዝዛል ።

ቅዳሴ እየተቀደሰ እንኳንስ በድምጽ ማጉሊያ ጩሆ መናገር በለሆሳስም ቢሆን መናገር ሕገ ወጥ ተግባር መሆኑ አያጠራጥርም ቤተ ክርስቲያን ዕርዳታ አትጠይቅ አትባልም ፣ የምትኖረው በዕርዳታ ነውና ዕርዳታ የመጠየቅ ግዴታ አለበት ፣ ነገር ግን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በድምፅ ማጉሊያም ሆነ በቃል የሚጠየቀው ዕርዳታ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ፈጽሞ መወገድ አለበት ።

ይህንንም ስንል በቅዳሴ ጊዜ ወንጌል ተነቦ ከተተረጐመ በኋላ የሚዞረውን ሙዳየ ምጽዋት አይገባም ማለታችን አይደለም ወንጌል ተተርጉሞ ሲያበቃ ወዲያው ሙዳየ ምጽዋት ማዞር ተገቢ ነው ያም ቢሆን የሚዞረው በድምፅ ሳይናገሩ እንጂ ዕርዱ እያሉ በመናገር አይደለም ።

ሕዝበ ክርስቲያኑ ለቤተ ክርስቲያናችን ዕርዳታ የሚያደርገው መላልሶ በድምፅ ማጉሊያ በመናገር ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ሊያደርገው የሚገባውን መንፈሳዊ ግዴታ በመገንዘብ ነው ።

ስለዚህ በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በድምፅ ማጉሊያና በቃል እየተጮኸ የሚጠየቀው ዕርዳታ ለጸሎተ ቅዳሴ የተሰበሰበውን ሕዝበ ክርስቲያን ከማበሳጨትና ከማስመረር በስተቀር ሌላ ጥቅምን የሚያበረክት አይመስለንም ፣ ይህንንስ ትቶ በጸሎተ ቅዳሴው መፈጸሚያም ሆነ ከመጀመሩ አስቀድሞ ትምህርተ ወንጌል በሚገባ ካስተማሩ በኋላ ዕርዳታ ቢጠየቅ ሕዝበ ክርስቲያኑ የተፈላገውን ዕርዳታ እንደሚያበረክት አይጠረጠርም ።

ስለዚህ የጥያቄውን መልስ ለማጠቃለል በቅዳሴ ጊዜ ከአንዱ ቦታ ተነሥቶ ወደሌላው መዘዋወርና በድምፅ ማጉሊያም ሆነ በቃል እየጮሁ ዕርዳታ መጠየቅ ከቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት ውጭ በመሆኑ ማንኛውም ዕርዳታ ጠያቂ በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በድምፅ ማጉሊያም ሆነ በቃል ከሚያደርገው ልመና እንዲቆጠብ ስናሳስብ ይህም በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የተደገፈ መሆኑን ጭምር በማገለጽ ነው ።

ጠያቂው ስመዎን በመደበቅዎ በጣም እያዘንን አጠቃላይ ትምህርት ሰጥተን በታል ስመዎን ቢገልጹ ኑሮ የሚመለከተውን ክፍል ጠይቀን ተገቢውን እርማት ለመስጠት እንችል ነበር ።

ለትንሣኤ መጽሔቶ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

እኔ ሰላማዊት እባላለሁ ዕድሜዬ ሃያ ሁለት ሲሆን በንግድ ሥር ት/ቤት በቀን ተማሪነት በመማር ላይ ነኝ የትንሣኤን

ወደ ገጽ ፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርዕሰ አንቀጽ

# ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ

ለመዋጥ የተለያዩ መንገዶች አሉት አንድ ሰው ሊወጣው የማይችለው የችግርና የዕዳ አዘቅት ሲያጋጥመው በችግር ተዋጠ ይባላል ። በእግር ወይም ዋኝቶ ሊሻገረው ከማይቻለው ባሕር ወይም ረግረግ የገባ ሰውም ተዋጠ ይባላል ፣ ለምግበ ሥጋና ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ነገሮችም ይዋጣሉ ።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የምንፈልገው ከዚህ በላይ ስለተጠቀሱት ሳይሆን ስለሞት መዋጥ ነው ሞት ከተጀመረበት አንስቶ እስከ ክርስቶስ ትንሣኤ ድረስ የአዳምን ልጆች ሁሉ ሲውጥ ኑሯል ። ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ ግን ሁሉን ሲያሸንፍ የነበረው ሞት በመሸነፍ ባሕር ተውጧል ጥላ ቀን በፀሐይ ወቅት ሰውን ሲከተል ይውልና ፀሐይ ሲጠልቅ ወይም ሰውዬው ወደቤት ሲገባ የደረሰበት እንደሚጠፋ ሞትም አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሙሉ በሰው ልጆች ላይ ሠልጥኖ ኑሮ በክርስቶስ ትንሣኤ ድል ስለተመታ ድራሹ ጠፍቷል ።

ጥንቱንም ቢሆን እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረውም አምላክ ማነኛውም ፍጡር እንዲኖር መኖሪያውን ጭምር በሚገባ ፈጥሮ አዘጋጅቶ ሰጠው እንጂ ከዚህ ዓለም ኑሮው የሚለይበትን ሞትን አልፈጠረውም ሞት የተፈ ጠረው በቃኤልና በአቤል መካከል በተነሣው ጥላቻ ነው ።

ታሪኩ ዘለግ ያለ ቢሆንም ስለሞት አጀማመር በአጭሩ መመልከት ተገቢ ይመስለናል ፣ አቤልና ቃኤል ወንድማማቾች ሲሆኑ ሥራቸው የተለያየ ነበር አቤል በግ ጠባቂ ቃኤል ገበሬ በመሆን የዕለት ተግባራቸውን ያከና ውኑ ነበር ።

ከዕለ:·ት አንድ ቀን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ ተዘጋጁ አቤል ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ንጹሕ ነገርን ቢያቀር፡·ሉት ይወዳል አለና ከሚጠብቃቸው በጐች መካከል ጠጉሩ ያላረረውን ፣ ቀንዱ ያልከረከረውን፣ ጥ ፍሩ ያልዘረዘረውን ፣ የሰባውንና የወፈረውን ጠቦት መርጦ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ እግዚአብሔርም የአቤልን ቅንነትና የዋህነት ተመልክቶ መሥዋዕቱን ተቀበለለት ።

ቃኤል ግን መሥዋዕቱን እግዚአብሔር አይበላውም አለና ሳይመርጥና ሳይጠነቀቅ ሥንዴውን ከእንክርዳዱ አቀረበ ፣ እግዚአብሔርም የቃኤልን ተንኰል ተመልክቶ ያቀረበውን መሥዋዕት ሳይቀበልለት ስለቀረ በወንድሙ በአቤል ላይ በምቀኝነት ተነሣበት ። ከዚያ በፊት ሞት አይታወቅም ነበርና ፣ በመንፈሰ ሰይጣን በመመራት እሸት እንብላ ውሀም እንጠጣ ብሎ አቤል ወንድሙን አታሎ ወደበረሃ ወስዶ በደንጊያ ራሱን መትቶ ገደለው ፣ በዚህ ጊዜ ፣ ነው ሞት የተፈጠረው ። ዘፍ.፬.፰

ይህንንም መሠረት በማድረግ "እግዚአብሔርሰ ኢገብረ ሞተ አላ ረሲአን ሰብእ ጸውዕዎ ወአርከ ረሰይዎ ወአምሰልዎ" እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረውም ሕግን የዘነጉ ሰዎች ጀመሩት ጠሩት ወዳጅም አደረጉት ራሳቸውንም አስመሰሉት እንጂ ሲል ጠቢቡ ሰሎሞን ተናግሯል ።

ይህ ሞተ ሥጋ የተጀመረበት ጊዜ ሲሆን ሞተ ነፍስ ደግሞ ከዚያ ቀደም ሲል በአዳምና በሔዋን ተጀምሯል እግዚአብሔር አምላካችን ለሰዎች አገልግሎት የሚውሉትን ፍጥረታት ፈጥሮ ሲያበቃ በመጨረሻ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ያለውን ሁሉ እንዲጠቀሙበት ሲፈቅድላቸው የአንዲት እንጨት ፍሬን እንዳይበሉ አዝዞ ከዚያች የእንጨት ፍሬ ቢበሉ ግን የሞት ሞትን እንደሚሞቱ ነገራቸው ፣ የሞት ሞትም የተባለው ሞተ ነፍስ ነው ።

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቀው ሕጉን አክብረው ለመኖር አልቻሉም ከጥቂት ጊዜ በኋላ በእባብ አሳሳችነት የተከለከለውን የዕንጨት ፍሬ ቀጥፈው በሉ ፣ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጆች በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ሲኦል ተጨምሮባቸው በመንጸፈ ደይን ወድቀው ፣ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቀው መኖር ግድ ሆነባቸው ።

ቢሆንም ለአዳምና ለሔዋን ክርስቶስ ተወልዶ እንደሚያድናቸው የተስፋ ቃል ተነግሯቸው ስለነበር እነርሱና የልጅ ልጆቻቸው በተስፋው ቃል ሲጽናኑ ኑረዋል ።

ክርስቶስ እንደሚወለድና የሰውን ወገን ከፍዳ እንደሚያድን የተቆጠረው ሱባኤ ፣ የተነገረው ትንቢት እየተቃረበ ሲሔድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተወለደ ከተወለደም በኋላ የኦሪትን ሕግና ሥነ ሥርዓት ሳያፋልስ ቀስበቀስ አድጎ በ፴ ዘመኑ ተጠመቀና ሳይውል ሳያድር ዕለቱን ወደገዳም ሂዶ በዚያ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ ፡ በተራበም ጊዜ ሰይጣን በሦስት መንገዶች ተፈታተነው ።

፩ኛ/ በስስት ሁለተኛ በትዕቢት ሶስተኛ በፍቅረ ንዋይ ክርስቶስን ቢፈታተነው በሁሉም ድል ስለነሣው እንደ ትቢያ በኖ እንደጉም ትኖ ድራሹ ጠፍቷል ፣ ይሁን እንጂ ሰይጣን ድል ተነሥቶ እንደተባረረ አልቀረም በአይሁድ ላይ አድሮ በዕለተ ዓርብ አሰቅሎታል ፣ በሰሙነ ሕማማት የሚነበበው ግብረ ሕማማት እንደሚገልጸው በክርስቶስ ሞት ያልተባበሩ አይሁድ አይገኙም ሁሉም ተባብረው ክርስቶስን እንዲሰቅሉ ስለታዘዙ እኩሉ በሐሠት በመክሰስና በመመስከር ሌላውም የተንኰል ምክር በመምከር ፣ ከዚያ የተረፈው ሕዝብ ደግሞ በዚያን ጊዜ የነበረው ዳኛ ጲላጦስ ክርስቶስን መርምሮ ምንም በደል እንዳላገኘበት በተናገረ ጊዜ በደልም ባይገኝበት ዝም ብለህ ስቀለው በማለት ቃሉን አሰምቶ ጮኋል ።

ይሁን እንጂ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሥጋ የለበሰው ተሰቅሎ ሙቶ ለሰው ልጆች ዘለዓለማዊ ነፃነትን ለማጐናጸፍ ስለሆነ ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ በመስቀል ላይ ተሰቅሏል ። ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ በሰማይ ፀሐይ ጨልሟል ፣ ጨረቃ ደም ሆናለች ። ከዋክብትም እንደቅጠል ረግፈዋል ። በምድር ደንጊያዎች ተሰነጣጥቀዋል ። መቃብሮች ተከፍተዋል ሙታን ተነሥተዋል የቤተ መቅደስ መጋረጃም ከሁለት ተከፍሏል ።

ክርስቶስ ከ፮ - ፱ ሰዓት ድረስ በመስቀሉ ላይ ቆይቶ በዘጠኝ ሰዓት ኤሎሄ ፣ ላማ ሰበቅታኒ እያለ ሲጮህ አይሁድ ሰምተው ኤልያስን የሚጠራ ስለመሰላቸው ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደሆነ እስኪ እናያለን እያሉ ዘበቱበት ፡ ወዲያው ከመካከላቸው አንዱ ባዘቶ አመጣና በዘንግ አሥሮ ሆምጣጤ ከነከረ በኋላ ወስዶ ከመድኃኒታችን አፍ ጋር በማገናኘት ጨመቀው ኢየሱስም ያነን ገርገጭ አድርጐ "ወይቤ ተፈጸመ ኩሉ" ሁሉ ተፈጸመ ብሎ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለየ ።

በሥጋው ወደ መቃብር ሲወርድ በአካለ ነፍስ ወደሲኦል ወርዶ "በሲኦል ያላችሁ ውጡ በጨለማም ያላችሁ ወደ ብርሃን ተገለጡ" በማለት ነፃነትን ሰበከላቸው በዚያን ጊዜ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ የሞቱ ነፍሳት ሁሉ በጠቅላላ ከሲኦል ወደገነት ከጨለማ ወደ ብርሃን ተሸጋገሩ ፣

ይህንንም ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲገልጽ "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኔ ቤት ለነበሩ ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው" ብሏል ። ፩ኛ ጴጥ. ፫.፲፱ ።

ክርስቶስ ለአዳም የሰጠውን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሲል የተቀበለው መከራ እንኳን ለማየት ለመስማትም የሚዘገንን ነው ፣ ነገር ግን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ስለእኛ በደልና ኃጢአት ተላልፎ ለመሞት ስለሆነ የደረሰበትን መከራ ሁሉ በትዕግሥት ተቀብሎ ለእኛ ለወገኖቹ ዘለዓለማዊ ደኅነትን አጐናጽፎናል ።

ነቢዩ ኢሳይያስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል ስለተቀበለው ፀዋትወ መከራ ሲገልጽ "በእውነት እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንንም ተሸከመ እኛም እንደተመታ ቆጠርነው እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ተወጋ ስለ ዓመፃችን ተገረፈ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ አኖረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን ብሏል ኢሳ. ፶፫. ፬ ።

ከላይ እንደተገለጸው አሁን ሞት ድል በመነሣት ባሕር ተውጧል እንግዲህ ወዲህ ለሞት ኃይልና ሥልጣን አይኖረውም ፡ ኃይሉ በክርስቶስ ሞት ተደምስሷል ። ሥልጣኑም ተሽሯል ፣ ስለዚህ እንደገና ተመልሰን የኃጢአት ተገዥዎች እንዳንሆንና በክርክስቶስ ሞት ያገኘነውን የነፍስ ነፃነት እንዳናጣ ሕግጋቱንና ሞቱን በማሰብ ሕጉን ጠብቀን ትእዛዙን አክብረን መኖር ይገባናል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ" ብሏልና ገላትያ ፭.፩ ።





www.ethiopianorthodox.org

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

መጽሔት መከታተል ከጀመርኩኝ ከአምስት ዓመታት በላይ ሆኖኛል በመጽሔቱ እጅግ በጣም ጠቃሚዎች የሆኑ ትምህርቶችን አግኝቼበታለሁ ።

አሁን ልጠይቅ የምፈልገው በመንፈሳዊ ሕይወት ከሕፃንነት ወራት ጀምሮ እስከ አሁን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው ስሙ ከሚመሰገንበት ቃሉ ከሚሰማበት ቤተ ክርስቲያን ርቄ አላውቅም እንዲያውም ይበልጥ መንፈሴ ከሥጋዊ ምኞትና አሳብ ይልቅ በይበልጥ ወደመንፈሳዊ ሕይወት እያደላሁ መሆኔ ይሰማኛል ።

አሁንም በክርስቶስ ቃልና ትዕዛዝ ሥር በመሆን ሥጋውንና ደሙን በመቀበል ላይ ነኝ ዓላማዬ ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ በኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት አባል በመሆን ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በመሄድ ከተቻለ በድንግልና ፣ በንጽሕና ምንኩስናን ተቀብየ በዚያው ገዳም ውስጥ ቀሪ ዘመኔን ለመፈጸም እጅግ በጣም ጥልቅ የሆነ አሳብ አለኝ ።

ይህንንም መመኘቴ የሚደርስብኝን ፈተናና መከራ ባለማሰብ አይደለም መጻሕፍትን ለማንበብ ዕድል ገጥሞኛል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ተከተለኝ" ያለውን በማሰብ ፍጹም እርሱን ክርስቶስን መስዬ ከዚህ ዓለም ለማለፍ ነው ምኞቴ ፤ ይህም ድንገተኛ ፍላጎት ሳይሆን ቀደም ብዬ ስመኘው የነበረ አሁንም ጧትና ማታ የማስበውና የምመኘው ነው በክርስቶስ ወንድሞቼ አሁን ልጠይቃችሁ የፈለግሁት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት አጥቢያ ውስጥ በዕድሜ የገፉ ካልሆኑ በስተቀር ልጅ እግሮች በእኔ ዕድሜ ያሉ መነኮሳት ከዚያ ለመኖር አይፈቀድላቸውም ሲሉ ስለሰማሁ ይህ ምን ያህል እውነት እንደሆነ እንድታብራሩልኝና እኔም በምን ዓይነት መንገድ ምንኩስናን ተቀብዬ በዚያ ለመኖር እንደምችል እንድትገልጡልኝ ስል በትሕትና እጠይቃለሁ ።

ለትብብራችሁ በቅድሚያ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ ትንሣኤ መጽሔትን አግኝቼ ለማንበብ ስለምችል መልሱን በአድራሻዬ ጽፋችሁ እንድትልኩልኝ በአክብሮት እለምናለሁ ።

ወ/ት ሰላማዊት ታምራት
ፖ.ሣ.ቁ. 4192
አዲስ አበባ

ወ/ት ሰላማዊት ታምራት ከአምስት ዓመታት ጀምረሽ የመጽሔታችን ተከታታይ መሆንሽን ስለገለጽሽልን እጅግ በጣም እናመሰግናለን ወደፊትም መጽሔታችን ከመከታተል ቸል እንደማትይና አንዳንድ መንፈሳዊ አሳብ ሲኖርሽም በጽሑፍ እንደምትገልጭልን ተስፋ እናደርጋለን ።

ከዚህ ቀጥሎ ለጠየቅሽው ጥያቄ መልስ እንሰጣለን ዕድሜሽ ሀያ ሁለት ዓመት ሲሆን ወደመንፈሳዊ ተግባር ማዘንበልሽ ያስመሰግንሻል ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ክፍል አንቀጽ አሥር ላይ ስለመነኮሳት ሕይወት በሚገባ ያስረዳልና ያነን ብታነቢ ሁሉንም ለመረዳት ትችያለሽ በተጨማሪም መጽሐፈ መነኮሳት ብትመለከች የመነኮሳትን ተግባርና ክብር ትረጃለሽ ።

የቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ ምንኩስና ከ30 ዓመታት በፊት እንዳይፈጸም ያዝዛል ይህንንም ማለቱ ክርስቶስ በሰላሳ ዘመኑ ስለተጠመቀ ያንን መሠረት በማድረግ ነው ። የማመዛዘን ችሎታም ቢሆን በሰል ሊል የሚችለው ሰውነት ጠንከር ሲል ነው አንችም ሳትቸኩይ ዝግ ብለሽ አመዛዝነሽ ነው የምንኩስና ተግባርን መጀመር ያለብሽ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ዕርፍን ይዞ ወደ ኋላ ማረስ የሚችል የለም" ብሎ እንደተናገረው ከመነኮስሽ በኋላ ተመልሰሽ እንዳትጸጸች አስቀድመሽ ማሰብ ማውጣትና ማውረድ አለብሽ ሉቃስ ፲ ፲፱-፲፬. ፳፰ ።

እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚቻለው በምንኩስና ብቻ እንዳይመስልሽ በድንግልና ፤ በንጽሕና ሆኖ ሳይመነኩሱ ወይም በትዳር ተወስኖ በዓለማዊ ግብርም በመሆን እግዚአብሔርን ለማገልገል ይቻላል "የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸው" ተብሎ ተጽፏልና ሉቃስ ፲፮.፰

አንች በምናኔው ልብሽ ከቆረጠ ግን ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ለመኖር ችግር የሚገጥምሽ አይመስለንም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ለብዙ ዓመት ኑረው ከተመለሱት አበው ጠይቀን ማንኛውም መነኩሴ በዚያ ለመኖር አይከለከልም የዕድሜ ገደብም የለውም ምንኩስናውን ግን ከዚሁ ከሀገራችን ተቀብሎ መሄድ አለበት በዚያ በገዳሙ ውስጥ ሲኖርም የሚችለውን ሥራ መሥራት ስላለበት አንድ ሥራ ይሰጠዋል ያነኑ የተሰጠውን ሥራ ሳይንቅና ሳያቃልል በሚገባ እየሠራ ለመኖር ይቻላል በማለት አስረድተውናል ።

ወ/ት ሰላማዊት ከልብሽ ቆርጠሽ ከተነሣሽ ወደመንበረ ፓትርያርክ ስብከት ክፍል ብቅ በይና በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በቃልም ጭምር ተገቢውን ምክር ለመለገሥ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፈቃደኛ ነው።



# ዳግም ምጽአት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጅ ደህንነት ራሱን መስዋዕት አድርጎ ዓለምን ለማዳን የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ወደዚህ ዓለም እንደመጣ ሁሉ በዚህ ዓለም መጨረሻም ዓለምን ለማሳለፍና ለጻድቃን ዋጋቸውን ለሐጥአን ፍዳቸውን የመጨረሻ ፍርድ ለመስጠት ዳግመኛ እንደሚመጣ በቅዱሳት መጻሕፍት ተረጋግጧል ። ይህም የጌታችን ለሁለተኛ ጊዜ መምጣት ዳግም ምጽአት ይባላል ሠለስቱ ምእትም ስለዚሁ ዳግም ምጽአት ሲያስረዱ በሕይዋንና በሙታን ላይ ፍርድን ይሰጥ ዘንድ ዳግመኛም በምስጋና ይመጣል ሲሉ በጸሎተ ሃይማኖት ተናግረዋል ።

ክርስቶስ በመጀመሪያ ጊዜ የመጣው ዓለምን ለማዳን ስለሆነ ስለሰው ልጅ በደልና ስሕተት ራሱን ክሶ በእሱ ውርደት የሰውን ልጅ ወደቀደመ ክብሩ መልሶታል ። በእሱ ቁስል ተፈውሷል በሞቱም ደህንነትንና ሕይወትን አግኝቷል ። መድኅን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ በዕለተ ምዕአት ጻድቃን ስለሚያገኙት ክብር ኃጥአንም ስለሚደርስባቸው የመጨረሻ ውድቀት ከማስረዳቱም በላይ ከዕለተ ምጽአት በኋላ የምንወርሳትን መንግሥተ ሰማያት ልናገኝ የምንችለው በእንዴት ያለ ዝግጅት እንደሆነ በትምህርቱ ገልጿል ። በመጨረሻም ሞትን ድል ነሥቶ ፤ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ከሙታን በመነሣቱ ለሰዎች ሁሉ በኩረ ትንሣኤ በመሆን በዕለተ ምጽአት ለሚነሡት ትንሣኤ ጀማሪና ፈጻሚ ሆኗል በተነሣ በ፵ ቀኑም ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ወደ ሰማይ በሚያርግበት ጊዜ ሐዋርያት ትኩር ብለው እየተመለከቱ ሳሉ የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል" ሲሉ መላእክት ነጫጭ ልብስ በለበሱ ሁለት ሰዎች ተመስለው በነገሯቸው መሠረት የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንደሚመጣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን ክርስቲያኖች ሁሉ በእምነት ይቀበሉታል ።

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በምግባርና በሃይማኖት ፀንተው ትሩፋት ሠርተው ትእዛዙን ጠብቀው በመኖር ዕለተ ምጽአትን ለሚጠባበቁ ደጋግ ሰዎች ዋጋቸውን ለመክፈል ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በትእዛዙ መሠረት ሃይማኖታቸውን ላልጠበቁና ከትእዛዙ ውጭ አፈንግጠው ለኖሩት ኃጥአን የመጨረሻ ፍርድን ለመስጠት በመሆኑ አመጣጡ እንደቀድሞው በውርደት ሳይሆን በግርማ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነው ።

በዳግም ምጽአቱ በክብር ዙፋኑን በተቀመጠ ጊዜም ለያንዳንዱ እንደ ሥራው ዋጋውን እንደሚከፍለው የተረጋገጠ ስለሆነ ስለዚህ የፍርድ ቀን ደግ የሠሩ ሲደሰቱ መጥፎ ለፈጸሙ ደግሞ እጅግ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነው ።

ወንጌላዊው ማቴዎስ በምዕራፍ ፳፭ ፡ ፴፩ - ፴፪ "የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክት ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል ። አህዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛ በጐችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስበርሳቸው ይለያቸዋል ። በጎችን በቀኙ ፍየሎችን በግራው ያቆማቸዋል" ካለ በኋላ በቁጥር ፵፮ ላይ ደግሞ በዚሑ ጊዜ ኃጥአን ወደ ዘለዓለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደዘለዓለም ሕይወት እንደሚገቡ ጌታችን ኢየሱስ ያስተማረውን በሰፊው ያብራራል ።

ይህ የሚሆነው መቼ ነው ?

ይህ ጥያቄ በብዙዎች ሕሊና ሲጉላላ የሚኖር ቢሆንም ጥያቄው አዲስ ሳይሆን ቃሉ ሲነገር በወቅቱ የነበሩት ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን ይህ መቼ ይሆናል ? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድነው ሲሉ አስቀድመው የጠየቁት ጥያቄ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ዕለቱንና ሰዓቱን ሳይሆን ምልክቶቹን ብቻ ነግሮ የእነዚያ ምልክቶች መፈጸም እያዩ ሰዎች ሁሉ ተዘጋጅተው እንዲኖሩ በብዙ ምሳሌና ማስረጃ ጭምር አስጠንቅቋቸዋል ማቴ ፳፬ ከቁጥር ፫ ፣ ፵፭ ።

የመምጣቱ ምልክቶች ምንድናቸው ?

እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚሉ ብዙ የሐሰት ክርስቶሶች መነሣታቸው በታሪክ ተመዝግቧል ሰላምና ፍቅር በዓለም ላይ ቀዝቅዞ በዓለም ላይ ፀብና ጥላቻ እየነገሠ መጥቷል እነዚህና የመሳሰሉት ምልክቶች እየተፈፀሙ በሚታዩበት ጊዜ እንጂ መቼ እንደሚሆን ቀኑንና ሰዓቱን ለይቶ ሊያውቅ የሚችል የለም ።ያችን ቀን ከአብ በቀር የሚያውቃት የለም ተብሎ ስለተጻፈ በዚህ ጊዜ ነው ለማለት እጅግ ያስቸግራል ?

ያም ሆነ ይህ ቀኑንና ሰዓቱን አታውቁምና ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሚል ማስጠንቀቂያ ስለተሰጠ ሰዎች ሁሉ በመልካም ምግባርና በሃይማኖት ፀንተው እንዲኖሩና በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለሚሠሩት ኃጢአትም በየጊዜው ንስሐ እንዲገቡ ያስፈልጋል ።

ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ



www.ethiopianorthodox.org

## የልማት ዓምድ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የተቋቋመበት መንፈሳዊ ዓላማ ግቡን ለመምታት እንዲችል የልማት ተግባሮች ፣ በተፈጥሮና



የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በኢልካ አዳራሽ

በሰው ሠራሽ ችግር የተጐዱትን ወገኖቻችን ለመርዳት የሚያስችለውን መንፈሳዊ አገልግሎት በግብር ለመተርጐም የቻለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ምክር ቤት እንደ ኤ.አ. ከ፲፱፻፸፪ ጀምሮ በሚለግሠው የገንዘብ እርዳታ ነው ።

በተለይም እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. ለቤተ ክርስቲያናችን ባደረገው የተቀደሰ መንፈሳዊ እርዳታ በአሥሩ አህጉረ ስብከትና በአዲስ አበባ ከተማ ጭምር ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችና በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግር ለተጐዱት ወገኖቻችን መርጃ በእርዳታ ላይ የዋለው ገንዘብ ከአንድ ሚሊዮን ተኩል በላይ መሆኑ ታውቋል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ምክር ቤት የልማት ክፍልና የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ተወካዮች የተገኙበት ዓመታዊ ስብሰባ ከመንግሥት በተፈቀደው መሠረት በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ከጥር ፪ - ፬ ቀን ፲፱፻፸፬ ድረስ በናዝሬት ከተማ በሚገኘው አዳማ ሆቴል ስብሰባ አድርጐ በልማት ፣ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግር ለተጐዱት ወገኖቻችን የተደረገውን እርዳታ ገምግሞና አመዛዝኖ እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. የተፈቀደው በጀት እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ድረስ እንዲቀጥል ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት እርዳታው እስከ አሁን ሲቀጥል መቆየቱ የተረጋገጠ ነው ።

እንዲሁም የ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ዓመታዊ ስብሰባ ከየካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፭ ጀምሮ እስከ የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ እንዲደረግ ከመንግሥት በተፈቀደው መሠረት ለሦስት ቀናት በ"ኢልካ" ተከናውኖአል ። ለሦስት ቀናት በ"ኢልካ" ሲከናወን የሰነበተው ይህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ምክር ቤት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባል ሀገሮች ተጠሪዎች ናየኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ የቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፣ የመምሪያ ኃላፊዎች ተሳትፈውበታል ።

ስብሰባው ያተኮረው በኢትዮጵያ ውስጥ አልፎ አልፎ ስለደረሰው ችግርና ቤተ ክርስቲያን በልማት በኩል ልትፈጽመው ስለሚገባት ተግባር ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ኅብረተሰቡን በሚገባ ለማገልገል እንዲችሉ ስለሚሠለጥኑባቸው ፣ አምስት የማሠልጠኛ ጣቢያዎችና ራስ አገዝ ስለሆነው የሰበካ ጉባኤ አደረጃጀት ዕቅድና አፈጻጸም በቀረበለት ግምገማ ላይ ጉባኤው በሰፊው ተወያይቷል ።

ከብዙ ውይይትም በኋላ ጉባኤው በመጨረሻ ለቀረቡለት ዕቅዶች ማስፈጸሚያ ለሁለት ዓመታት በተደረገው ስምምነት ብር ፬ ሚሊዮን ፯፻ሺ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ በጀት አጽድቋል ።

ጉባኤው በተለይም ለድርቅ ችግር ልዩ ትኩረት እንደሚሰጠው አረጋግጦ ባለፈው ዓመት ከተሰጠው በበጀት ከተያዘው ብር ፩፻፲፯ሺ ፫፻፵፰ የአራት መቶ አሥራ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ያላነሠ ዕርዳታ ለማዋጣት

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል



# ጾም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ሥርዓት

ቤተ ክርስቲያን ለአማኞቿ እንዲጾሙ በውሳኔ ያስተላለፈቻቸው አጽዋማት እንዳሉ ምስጢር ሳይሆን ግልጽ ነው ።

በቤተ ክርስቲያን ከጾሙ ጋር የሚካሔድ ሥርዓት አላት ሥርዓቱም በተመስጦ ስለሆነ ለአገልግሎት የተሰለፉት ካህናት ሌሊት በሰዓታት ቀን በማኅሌት ቆመው ሲታዩ ካህናተ ሰማይ ወደሚለው ስም ስለሚያመራ ትርጉሙ ቦታውን ሊይዝ ይችላል የሚል ግምት ይሰጠዋል ።

በዚህ ጽሑፋችን ለመግለጽ የፈለግነው የሌሎችን አጽዋማትና ሥርዓት ከማውሳት ተቆጥበን በዓቢይ ጾም የሚካሔደውን ሥርዓት በአጭሩ ለመግለጽ እንሞክራለን ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መጾም ከጀመረበት ቀን አስቀድሞ አንድ ሳምንት ጾመ ሕርቃል እየተባለ ይጾማል ይህ ጾም በፍትሕ መንፈሳዊ በዝርዝር ከመቅረቡም ሌላ ቅዱስ ያሬድ ጾመ ድጓ በተባለው ድርሰቱ የመጀመሪያውን ሳምንት በመስጠት "ከላይ የወረደውን አይሁድ ሰቀሉት በቃሉ የሚያድን የሁሉ ጌታ መሆኑን ምንም አላወቁም ። ያለፈው ዘመን ይበቃችኋል ከዛሬ ጀምሮ ጹሙ ጸልዩ" ሲል በመድረሱና በማዜሙ ቤተ ክርስቲያን ይህን አብነት በማድረግ ጾመ ሕርቃል ከመግባቱ አስቀድሞ ከቅዳሜ ጀምሮ ከከበሮና ከጸናጽል ማኅሌት በመክልከል ዜማዎቹን በዝማሬ ብቻ ስታካሒድ ትገኛለች ።

በቤተ ክርስቲያን ያለው ሥርዓት ከሰኞ እስከ ዓርብ ፣

የቅዱስ ያሬድን ድርሰት መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያን በአራት ክፍል ለእግዚአብሔር ምስጋና ታቀርባለች ።

ሀ/ የነግህ (የጧት)
ለ/ የሠለስት (የሦስት ሰዓት)
ሐ/ የስድስት (የስድስት ሰዓት)
መ/ የዘጠኝ ሰዓት እያለች የጾመ ድጓውን ዜማ ከምዕራፍ ዜማ ጋር በማዋሐድ ትዘምራለች ።

በነግህ የሚቆመው አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማያዝ የተማከሩበትን ለማስታወስ ሲሆን በሦስት ሰዓት የሚዘመረው ደግሞ ከያዙት በኋላ ወደ ቀራንዮ አደባባይ የሚሰቀልበትን ግንድ አሸክመው መሔዳቸውን የሚገልጽ ነው ።

የስድስት ሰዓቱም መድህን ክርስቶስ በደል ሳይኖርበት እንደ በደለኛ ተቆጥሮ በመስቀል ላይ የተሰቀለበትን ለማዘከር የሚካሄድ ሥርዓት መሆኑ ይታመናል ።

በመጨረሻ የሚዘመረው የዘጠኝ ሰዓት ደግሞ የዓለም ቤዛ ክርስቶስ "ሁሉም ተፈጸመ" ብሎ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው የለየበት ሰዓት መሆኑን ለማጠየቅ የሚዘመር ስብሐተ እግዚአብሔር ነው ሲሉ የዜማ ሊቃውንት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ ።

ከዚህ በላይ ያቀረብናቸው በየሰዓቱ ለምን እንደሚዘመሩ አጠቃላይ ትርጉማቸውን ለመግለጽ እንጂ የቅዱስ ያሬድን ድርሰትና ዜማ መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያን ለስምንቱ ዕለታተ ሰንበት የተለያየ ስም ሰጥታ ከእሑድ እስከ እሑድ በማኅሌትና በቅዳሴ ስታስታውሳቸው ትውላለች ።

የመጀመሪያውን ሳምንት ግን በመግቢያው መታሰቢያነቱ ለማን እንደሆነ ስለተገለጸ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከጾመበት ቀን ጀምሮ በምን ላይ እንደመሠረተ ፣ በቤተ ክርስቲያን ያለውን ስያሜና ሥርዓት እንመለከታለን ።

፩ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾሙን የጀመረበትን ቀን ቅዱስ ያሬድ በድርሰቱና በዜማው ዕለተ ሰንበት የዕረፍት ቀንና ከሌሎች ዕለታት የተለየች መሆኑን በግልጽ ሲያስረዳ "ሰንበት ቅድስት ለውሉደ ሰብእ መድኃኒት ለሙታን መንስኤ ከዕለታት ልዩነት ያላት ሰንበት ለሰው ልጆች መድኃኒት ናት ለሙታንም መነሻ ናት" ሲል ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ካወሳ በኋላ በሌላ በኩል ደግሞ በቅዱስ ወንጌል ያለውን ጠቅሶ "ብልና ዝገት በማያጠፋው ሌባ ቆፍሮ በማይወስደው በሰማያት መዝገብ ይኑራችሁ" እያለ የተናገረውን በመደገፍ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት በተባለው ዕለተ ሰንበት ትባላለች ይህም የመወደስ ቁመት በመባል ይጠራል የማኅሌቱም ሥርዓትየሚካሔደው በታላላቅ አድባራት ቅዳሜ ለእሑድ ከሌሊቱ አራት ሰዓት ጀምሮ እስከ ጧቱ አንድ ሰዓት ወይም ቅዳሴ እስኪገቡ ድረስ ነው ።

ሥርዓቱም በጸሎት ከተከፈተ በኋላ "በይእቲ ማርያም ዜማ ተጀምሮ በአቡነ ዘበሰማያት" ዜማ ይፈጸማል ። ይህ በዚህ እንዳለ ከሰኞ እስከ ዓርብ ያለው ሥርዓተ ማኅሌት ዕለተ ሰንበትን ሳያነሣ ቅድስት የሚለውን ቃል እያንፀባረቀ ከነግህ እስከ ቅዳሜ መግቢያ ድረስ ይዘመራል የመጠሪያ ስሙም የጾመ ድጓ ቁመት ይባላል ።

የቅዳሜው ቁመት ግን ቅድስትንና የጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት እያስተባበረ የያዘ ድርሰት ከመሆኑም በላይ ሥርዓቱም የሚካሔደው በነግህ ብቻ ነው ።

፫ኛው ሳምንት ምኩራብ በመባል ይጠራል ። እንደ ቅዱስ ያሬድ ድርሰት ጌታ ኢየሱስ በአይሁድ ምኩራብ ተገኝቶ የሰንበት ጌታና የምሕረት አባት መሆኑን ያስተማረበት ዕለት ነው ሲል በመዘመር ያስረዳል ።

ቤተ ክርስቲያንም ይህን መሠረት በማድረግ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ጀምሮ ማኅሌታውያን በቁመት ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ጾመ ድጓውንና ምዕራፉን ተከትለው መድኅን ክርስቶስ ሲያስተምር የቃሉን ጣፋጭነት የአንደበቱን



www.ethiopianorthodox.org

ቅልጥፍናና ሰንበትን አብሮ በማጣመር ሲዘምሩ ሌሊቱን ያነጋሉ ቀሳውስቱም ሰዓታቱንና መስተብቁውን ሊጠኑንና ኪዳኑን ሲያደርሱ ያድራሉ ለቅዳሴ መግቢያም የተወሰነው ሰዓት ሲደርስ የተመደቡት ቀሳውስትና ዲያቆናት ሥርዓተ ቅዳሴውን አከናውነውና ሥጋወደሙን አቀብለው ምእመናኑን ያሰናብታሉ ።

በተለይ በምኩራብ ዓርብ ምህላ ይባላል ። ይህም ሁለት ሳምንታት ከአለፉ በኋላ እንደሱባኤ ማሳሰቢያ ሆኖ የሚቀርብ ነው ። በዚህ ቀን ከዳዊት ማስተዛዘልና ከጥሬ ዜማ በቀር ዝማሜ እንኳን አይዘመም ቅዱስ ያሬድም "ተማኅለሉ ወሰዓሉ ኀበእሉክሙ እስመአብ ይሁበከሙ ኩሎ ዘሰአ ልክሙ" ወደ አባታችሁ ምህላ ያዙ የለመናችሁትን ሁሉ ይሰጣችኋልና" የሚል ቃል ነው።
የደረሰው

፫ኛው ሳምንት መፃጉዕ ተብሎ ይጠራል መጻጉዕ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታላቅ የታሪክ ምዕራፍ የያዘ ሆኖ ይገኛል ። ታሪኩንም በምንመለከትበት ጊዜ ቤተ ሳይዳ በተባለችው ሥፍራ አጠገብ አንድ መጠመቂያ ቦታ ነበረች በዚህችም ሥፍራ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በትእዛዘ እምላክ ወርዶ ውሃውን በሚያናውጥበት ጊዜ ቀድሞ የገባ ከበሽታው ይፈወስ ነበር መፃጉዕ ግን በሽታው በጣም የበረታ በመሆኑ ሔዶ ለመጠመቅ ዓቅም ስለሌለው ፴፰ ዓመት ሙሉ በአልጋ ላይ ይኖር ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ሲያልፍ አንተ ሰውልትድን ትወዳለህን ? ብሎ ጠየቀው መፃጉዕም እኔስ ልድን እወዳለሁ ግን ውሃው በሚናወጥበት ጊዜ ወደመጥመቂያው ቦታ ማን ቀድሞ ያስገባኛል ? አለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እምነትህ አድኖሃል ። አልጋህን ተሸክመህ ሒድ ስለአለው ወዲያው ድኖ አልጋውን ተሸክሞ ሔዶአል ።

ቅዱስ ያሬድም ይህን መነሻ በማድረግ ነው መንፈሳዊ ድርሰቱን ያዘጋጀው ከድርሰቶቹም አንዳንዶቹን ብንጠቅስ "ኢየሱስ መፃጉዕን አዳነው የዳነበትም ቀን ሰንበት ነው ። ኢየሱስ መፃጉዕን አልጋህን ተሸከመህ ሒድ ሲለው ያንጊዜ ሰንበት ነበር እርሱም አልጋውን ተሸክሞ ወደቤቱ ገባ" የሚሉ ይገኙባቸዋል ። ቤተ ክርስቲያንም በየዓመቱ ጾም በገባ በ፬ኛው ሳምንት መፃጉዕ በማለት በታላቅ ክብር ታስበዋለች በማኅሌትም በኩል ከሌሎች የጾም ዕለታት ለየት ባለ ሁኔታ "ጐሥዓ ልብየ" በተባለው የምዕራፍ ዜማ ላይ ጣዕም ያለውን የዝማሜ ሥርዓት ታካሒዳለች የሳምንቱም ቀለም የነርሱን ታሪክ የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን ።

፬ኛው እሑድ ደብረ ዘይት ሲሆን ይህ ቀን እንደቅዱስ ያሬድ ድርሰትና እንደ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አነጋገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጨረሻ ጊዜ ለፍርድ የሚመጣበት ቀን መሆኑን የሚያስታውሰው ነው ።

ቅዱስ ያሬድም ድርሰቱን ያዘጋጀው የወንጌሉን ቃል መሠረት በማድረግ በምሽት ፣ በመንፈቀ ሌሊት ፣ በጧት ፣ ይመጣ ሰዓቱን አታውቁምና ተዘጋጅታችሁ ኑሩ" ሲል መንፈሳዊ ድርሰቱን አዘጋጅቷል ።

ቤተ ክርስቲያንም ጌታችን ለፍርድ የሚመጣበት ቀን መሆኑን በማስታወስ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የማኅሌቱን ሥርዓት በማካሄድ ብቻ ሳትቆጠብ ታቦት በማንገሥ ታከብረዋለች ። ታስበዋለችም የዓቢይ ጾምም መንፈቅ (እኩሌታ) መሆኑንም ትመሰክራለች ከላይ እንደተጠቀሰውም ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ጀምሮ እስከ ሳምንት ድረስ የማኅሌቱም ቀለም የጌታን መምጣት የሚያበስር ነው ።

፭ኛው እሑድ ገብርኄር ይባላል ገብርኄር በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፭ ፣ ቁ. ፲፬ ላይ እንደምናገኘው ታማኙ አገልጋይ አምስት መክሊት ተቀብሎ ፭ት አትርፎ በማቅረቡ በጌታው ዘንድ ታማኝነቱን አስመስክሮአል ።

ይህን በማስመልከት ቅዱስ ያሬድ "መልካም ሥራ እየሠራ የሚያገኘው ታማኝ አገልጋይ ማን ነው ? ይህን ለሚያደርግ ጌታው በሁሉ ገንዘብ ላይ ይሾመዋል በማለት አብራርቶ ጽፎአል ።

በተለይ በቤተ ክርስቲያን የሚካሔደው የዜማ ስልት ከሌሎች ዜማዎች ለየት ብሎ እናገኘዋለን ። ለምሳሌ ዕዝል መደበኛ ዜማ ሲኖረው ከምኩራብ ሰኞ ጀምሮ ርእሱ ዕዝል ብሎ ዜማው ግን ግእዝ ነው ። ይህም "እምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወለምንት ኃደገኒ አጽምዕ እግዚኦ ዕዝነከ ወስምዓኒ" በሚለው የዜማ ለውጥ የገባ ነው ፣ እያሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ ። ዜማውም የሚመስጥ ነው ።

ከዚህም ሌላ ሦስተኛ ሳምንት በመሆኑ ረቡዕ የገብርኄር ምህላ ይባላል በዚህም ቀን በምኩራብ እንደተገለጸው ዝማሜ ሳይኖር በዜማ ብቻ ምህላውን ሲካሔዱ ይውላሉ ። ሌላው ሥርዓት ግን ከሌሎች ሳምንታት የተለየ አይደለም ።

፮ኛውን ሰንበት ቤተ ክርስቲያን ኒቆዲሞስ በማለት ትጠራዋለች በዮሐ. ወን.ም.፫ ፡ ቁ.፩ ፡ እንደምንመለከተው የአይሁድ መምህር የነበረ ኒቆዲሞስ የሚባል ሰው ነበር እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ ሔዶ መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው ።

ኢየሱስም መልሰ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ባለው ጊዜ ኒቆዲሞስ ስለአልገባው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ሲል አስረድቶታል ።

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም የአይሁድ አለቃ የነበረ ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ኢየሱስ ሔዶ መምህር ሆይ እናምንብሃለሁ ከአብ እንደመጣህ እናውቃለን ። መምህር ትሆን ዘንድ መጥተሃል እያለ ጾመ ድጓ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



## ዜና ሊቃውንት

ሊቀ ጠበብት መስፍን ኃይለ ማርያም ከአባታቸው ከአቶ ኃይለማርያም ታፈሰና ከእናታቸው ከወለተ ጊዮርጊስ አድገህ በሸዋ ክፍለ ሀገር በአጣዬ አውራጃ ኤፍራታ ልዩ ስሙ ካብ ሥላሴ ከሚባለው ቦታ በ1900 ዓ.ም. ተወለዱ ፡

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በዚሁ ስሙ በተጠቀሰው ደብር ከአለቃ ወልደ ገብርኤል ዘንድ ገብተው ዳዊትና ንባብ ተምረው በዚሁ ደብር በዲቁና ለ፬ ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ በ1917 ዓ.ም. ወደ ጐንደር ክፍለ ሀገር ሄደው በደብረ ታቦር አውራጃ ሞግሽ ኪዳነ ምህረት ከመሪጌታ ሰርጎወርቅ ጸዋትወ ዜማና ድጓ አጠናቀው ተምረዋል ። በዚሁ ደብር ከአለቃ አስካልቅኔን ከነአገባቡ በሚገባ ተምረው እንደገና የድጓ መመስከሪያ ወደ ሆነችው ቤተልሔም ወርደው ከአለቃ መርሻ ድጓውን አስመስክረው በድጓ መምህርነት ተመርቀው ከጨረሱ በኋላ ጐንደር ከተማ የ፵፬ቱን አድባራት ይትበሃሎች ለመቅሰም ድጓ እያስተማሩ ለ፯ ዓመታት ያህል ብዙ ደቀ መዛሙርትን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል ።

ወደ ወገራ በመሄድ ፫ት ጳጳሳትና ፯ እጨጌዎች ተቀብረውበት የነበረውን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በጠፋ በ፩፻፺ ዘመኑ እንደገና ዱሩን መንጥረው በአካባቢው ያሉትን ምዕመናን አስተባብረው ሕንፃውን እራሳቸው አንፀው የተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን ሰርተው ፰ ዓመት ሙሉ በማስተማርና ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ብዙ ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም መዘምራን አውጥተው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አትርፈዋል ደቀመዛሙርቶቻቸውም አሁን በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።

በ፲፱፻፵፬ ዓ.. ከጐንደር ወደ ትውልደ ሀገራቸው ተመልሰው በታላቁ ካቴድራል በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ በድጓ መምህርነት ተቀጥረው ሲያስተምሩ ብዙ የሥራ ፍሬ ስላሳዩ ስለ መልካም ተግባራቸው በጊዜው ከነበሩት ከደብሩ አስተዳዳሪ የወርቅ ካባና ቀሚስ ጥንግ ድርብ ተሸልመዋል ።

በታማኝነታቸውም የካህናቱን መብትና ንብረት በመጠበቅና በማስጠበቅ ከ፲፱፻፶፱ እስከ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ድረስ በገንዘብ ያዥነት ሲሰሩ ዜሮ አምስት ሣንቲም ጉድለት አልተገኘባቸውም ።



ሊቀ ጠበብት መስፍን እኒህ ነበሩ

ሊቀ ጠበብት መስፍን ኃ/ማርያም በትምህርት ብቻ ሳይሆን በተግባረዕድም ትምህርት በኩል በጣም የሰለጠኑ በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያኑን ንዋያተ ቅድሳት እንደ መቋሚያና ጸናጽል ያሉትን ያለ ምንም ክፍያ በነፃ በመሥራት በጐ አገልግሎት ን አበርክተዋል ።

በሥራ መደባቸው ላይ በአሳዩት ከፍተኛ ትጋትና ጥረት ደቀመዛሙርቶቻቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ እውቀት እንዲያገኙ ከማድረጋቸው የተነሣ ከፍተኛውን የድጓ መጽሐፍ ለደቀመዛሙርቶቻቸው አሸልመዋል ።

ስለ መልካም አገልግሎታቸው ከቤተ መንግሥት ለሁለት ጊዜያት ካባና ልዩ ልዩ ሽልማቶች ተሸልመዋል ። በአገልሎታቸው ተመርጠው በዚሁ ካቴድራል ከዚህ የሚከተሉትን የሹመት ማዕረጋት ተቀብለዋል ።
፩ኛ. ቀኝ ጌትነት
፪ኛ. ርዕሰ ደብርነት
፫ኛ. ሊቀ ጠበብትነት
፬ኛ. ሊቀ ጉባዔነት በየደረጃው ተሹመዋል ።

በዚሁ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በቅንነትና በታማኝነት በጠቅላላው ለ፴፩ ዓመታት ያህል አገልግለዋል ። እንዲሁም ሊቀ ጠበብት መስፍን ኃይለማርያም አላማዊ ኑሮ ሲያምራቸው በድንግልና ጸንተው ከቆዩ በኋላ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ምንኩስናና ቅስና ተቀብለዋል ።
ኋላ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. በቅድስት ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ምንኩስናና ቅስና ተቀብለዋል ።

በበጐ አድራጐትም በኩል ገንዘባቸውን ላስቀምጥ ወይም ለግል ጉዳይ ላውለው ሳይሉ ብዙ ችግረኞችን እየረዱ አባትና እናት የሌላቸውን እያሳደጉ እያስተማሩ ከቁም ነገር ያደረሱ አባት ናቸው እንዲሁም ከየክፍለ ሀገሩ የሚመጡትን እንግዶች እየተቀበሉ በማስተናገድ ልዩ ልዩ ትሩፋት የሠሩ ደግ ርኅሩህ አባት ነበሩ ።

እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ፍጻሜው ያምራል በሚሞትበትም ቀን ይከብራል ሲራክ ም.፩ ቁ ፲፫ ።

እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ፈቃዱን ይፈጽማሉ የሚወዱትም ሰዎች ሕጉን ይጠብቃሉ ሲራክ ፪፡፲፮ ።

ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለ እናምናለን ። ፪ኛ ቆሮ ፭፡ቁ፩ ወአንሰ ወዳዕኩ ወሠለጥኩ ወበጽሐኒ ዕድሜዩ ለአዕርፎ ሠናየ ገድለ ታገደልኩ በድርየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖትየኒ አቀብኩ እንከሰ ጽኑህ ሊተ አክሊለ ጽድቅ ዘየአስየኒ እግዚአብሔር ይእተ ዕለተ መኰንን ጽድቅ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከገጽ ፮ የዞረ

ና ለደረሰው ችግር ሁሉ ተካፋይ ለመሆን ቃል በመግባት ስብሰባው ተደምድሟል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና የክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ከተቋቋመ ጥቂት ዓመታት ቢያልፍም ምንም እንኳን እየሠለጠኑ ናቸው ።

፱. የሰበካ ጉባኤ በሚገባ እንዲደራጅ ብርቱ የሆነ ጥረት ተደርጓል አሁን ሥራውን በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ነው ።

፲. ለስደተኞች ገንዘብ እየከፈለ ድርጅቱ ትምህርት እንዲማሩ ከማድረጉም ሌላ ወደ መኖሪያ ሀገራቸው ለሚመለ እንዲጠገኑና እንዲሠሩ አይድርጓል ወደፊትም ከላይ በተጠቀሱት የሥራ መሥመሮች ድርጅቱ ሥራውን ይቀጥላል ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው ።

ከ፩ - ፮ ተዘርዝረው የተነገሩትን ተግባራት በማከናወን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ እ.ኤ.አ. ከ፲፱፻፸፯ - ፲፱፻፹፫ ድረስ ፩ ሚሊዮን ፭፻ሺህ አንድ ሚሊዮን አም



የኢ.ኦ.ተ. ቤ.ተ.ክ. ሊቃነ ጳጳሳት በጉባኤው ላይ

የሚፈለግበትን ሠርቷል ተብሎ ባይመስገንም ባለው አቅሙ መንቀሳቀሱን ያቋረጠ አይመስለንም ። በተለይ እ.ኤ.አ. ከ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. ወዲህ አሠራሩን በማደስ በነበረው አሠራር ላይ ሌሎችንም ጨምሮ በመሥራት ላይ መሆኑ እሙን ነው ። እ.ኤ.አ. ከ፲፱፻፸፪ - ፲፱፻፹፫ ድረስ የተሠሩትን ዋና ዋና ሥራዎች እንዲገልጹልን የልማትና ዕቅድ አማካሪ አቶ በርሄ በየነን ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል ።

፩. ለኢትዮጵያ ሕብረተ ሰብእ ዋናው ክፍል ካህናትን በልማት ተግባር ማሠልጠን መሆኑንየዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ምክር ቤት በማመን እርዳታውን ስለለገሠን ቀደም ሲል ተጀምረው የነበሩት አምስቱ የካህናት ማሠልጠኛዎች በተሻሻለ መንገድ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጐ አሁን በጥሩ ሁኔታ ሱም ትራንስፖርትና ሌላም የሚያስፈልጋቸው ካለ ፣ እንዲሞላ ያደርጋል ።

፩. በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ችግር ደርሶባቸው ለተጐዱ መጠለያ ምግብና ልብስ በመስጠት ለጊዜው ከደረሰባቸው ችግር እንዲያገግሙ ፣ ያደርጋል እንዲሁም ከስደት ለተመለሱም ይህንኑ የመሰለ እርዳታ በማድረግ ይረዳል ።

፭. መሠረተ ትምህርት እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ማይምነት ከኢትዮጵያ ገጸ ምድር ፈጽሞ እንዲጠፋ በሚደረገው ጥረት በመተባበር ከአዲስ አበባ ከተማና ዙሪያ እስከ መቶ ኪሎ ሜትር ድረስ ራቅ ብሎ ወንበሮችንና ጥቁር ሰሌዳዎችን ሌሎችንም የትምህርት መሣሪያዎች በማቅረብ ይረዳል ።

፮. በክፍለ ሀገሩ ሊቀ ጳጳስ ተጠንተው ለተላኩልን አብያተ ክርስቲያናት ለጥገናና ለሥራ የሚሆን ገንዘብ ድርጅቱ እየሰጠ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ስት መቶ ሺህ ብር በላይ አውጥቷል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ምክር ቤት በዘንድሮውም ስብሰባ ላይ ብር 2ሚሊዮን ፯፻ሺህ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ለመስጠት ቃል ስለገባልን የተሰጠው ተስፋ ሲፈጸም ከላይ ከተጠቀሉት የበለጡ ሥራዎችን ለመሥራት እንችላለን ሲሉ አቶ በርሄ በየነ ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ በአሁኑ ጊዜ ለመሥራት የጀመረችው መንፈሳውያን ሥራዎች እጅግ በጣም አድካሚዎችና በርከት ያሉ በመሆናቸው ኃይሉንና ብርታቱን ጥበብንና ፈሊጥን እግዚአብሔር እንዲሰጠው እንመኝለታለን ።

ቁ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



## ታላቁ ያዕቆብ

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያዕቆብ በመባል የሚጠሩ ብዙዎች ናቸው ። በሐዋርያትም መካከል ሁለት ያዕቆቦች አሉ ። እነዚህም የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ ናቸው ሐዲስ ኪዳን እነዚህን ለመለያየት እያንዳንዳቸውን ከአባቶቻቸው ስም ጋር ይጠራቸዋል ። ከዚህም ሌላ ታናሹና ታላቁ የሚባለው የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ነው። ታላቁ የሚባለው ደግሞ የዘብዴዎስ ልጅ የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ነው ።

ታላቅ መባሉ የዘብዴዎስ መጀመሪያ ልጅ የዮሐንስ ታላቅ ወንድም በመሆኑ ሊሆን ይችላል ። በተጨማሪም አንድ ጊዜ ከወንድሙ ከዮሐንስ ጋር ሆኖ ሹመት ለማግኘት ጌታን ጠይቆ ነበርና ስለዚህ ታላቁ ተብሎ ይሆናል /ማቴ፳፥፳-፳፯/ ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ታላቅ ሊያሰኘው አይችልም ከጥንት ጀምሮ በክርስቲያኖች ዘንድ ታላቁ ተብሎ መጠራቱ በሐዋርያት አንድነት ውስጥ ከነበረው ከእልፍዮስ ልጅ ከያዕቆብ በዕድሜ ታላቅ በመሆኑና አስቀድሞ በመጠራቱ ነው ። ከዚህም ጋር ከሐዋርያት ሁሉ አስቀድሞ በሰማዕትነት በመሞቱ ታላቁ ያዕቆብ ሊባል ችሎአል ። አንዳንድ ሊቃውንት ግን ታላቁ የሚባለው የጌታ ወንድም እየተባለ የሚጠራው ያዕቆብ ነው ይላሉ ምክንያቱም ሲሰጡ የኢየሩሳሌም ኤጲስቆጶስና የመጀመሪያው ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ስለሆነ ነው ይላሉ ። ይሁን እንጂ ይህ አስተያየት በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም ።

ቅዱስ ያዕቆብ የምሥጢር ደቀመዛሙርት ከሚባሉት አንዱ ነው ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት ሲያስነሣ በደብረ ታቦር ላይ ምሥጢረ መንግሥቱን ሲገልጥ በጌቴሴማኒም ሲጸልይ ከወንድሙ ከዮሐንስ ከጴጥሮስ ጋር አብሮ ነበርና /ማር ፭፥፴፯-፵፫ ።ማቴ፥፲፯፥፩-፱ ፳፮፥፴፯-፵፮/

ያዕቆብ በትምህርቱ ጥልቅ ወልደ ነጐድጓድ ተብሎ ተሰይሞአል/ማር.፫፥፲፯/ ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማርያ ለመሄድ በፈቀደ ጊዜ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ በቅድሚያ ወደ ሰማርያ ሄደው የክርስቶስን ወደዚያ መምጣት እንዲነግሩ ተልከው ነበር። የሰማርያ ሰዎች ግን ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም ። በዚህ ጊዜ እነ ያዕቆብ ተመልሰው እሳት ከሰማይ ወርዶ የሰማርያ ሰዎችን እንዲበላቸው ጌታን ጠየቁ ። ይሁን እንጂ እነ ያዕቆብ ይህን የተመኙ በሥጋዊ ጠባይ በመሆኑ ጌታችን አልፈቀደላቸውም ። (ሉቃ ፱፥፶፪ - ፶፮ ።

ታላቁ ያዕቆብ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ በሐዋርያት ስም ዝርዝር ውስጥ ከመጠቀሱ በቀር ሰፋ ያለ ታሪክ ለብቻው አልተጻፈለትም ። የእንድርያስ ታሪክ በወንድሙ በጴጥሮስ ታሪክ የተሸፈነ እንደነበረ የያዕቆብ ታሪክም በወንድሙ በዮሐንስ ሥራና ታሪክ ተሸፍኖ ይታያል ። ምክንያቱም ከሁለቱም ወንድማማች ታሪክ የአንደኛው የዮሐንስ ታሪክ ጐልቶ ይታያልና።እርግጥ ያዕቆብ ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ዓሣ አጥማጅ እንደነበርና ዓሣ ከማጥመዱ ይልቅ የኃጢአት ባሕር ከሆነው ከዚህ ዓለም ሰዎችን እንዲያወጣ መጠራቱ ተገልጦአል።(ማቴ ፬፥፳፩) በመጨረሻም በሄሮድስ አግሪጳ ትእዛዝ በሰይፍ መገደሉን የሐዋርያት ሥራ በሁለት ቁጥሮች ላይብቻ ያስረዳል/የሐዋ ፲፪፥፩-፪/

ነገር ግን በትውፊት እንደሚነገረው ለታላቁ ያዕቆብ ከዚህ ሌላ ብዙ አስደናቂ የሆነ ታሪክ አለው ይህም እንደሚከተለው ነው ። ታላቁ ያዕቆብ ስለ ክርስቶስ ጌትነት አምላክነትና አዳኝነት በመመስከሩ ያላመኑት እንዲያምኑ ያመኑት ደግሞ በእምነት ጸንተው እንዲኖሩ አንድ አይሁዳዊ ወደ ፍርድ ሸንጎ በክስ አቀረበው።ነገር ግን ቅዱስ ያዕቆብ ከፍርድ ሸንጎ እንደቆመ በክርስቶስ ሳያፍር ሊፈርድ የተሰጠውንም ሳይፈራ ስለ ክርስቶስ በሚናገርበት ጊዜ የከሰሰው አይሁዳዊ በያዕቆብ ንግግር ልቡ ተነካ ያዕቆብን በመክሰሱ ተፀፀተ እሸቀሰ በያዕቆብ እግር ላይም ወድቆ ይቅርታን ጠየቀ ። ወዲያውም "እኔ እንደ ያዕቆብ ክርስቲያን ነኝ የያዕቆብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እምናለሁ" ሲል በአደባባይ አስታወቀ ። በዚህም ምክንያት ከያዕቆብ ጋር በሰይፍ እንደ ተገደለ አውሳብዮስ በቤተ ክርስቲያን መጽሐፉ ላይ መዝግቦአል።ይህም ትክክለኛና ሊታመን የሚገባ ታሪክ ነው ።

ከዚህም ሌላ ቅዱስ ያዕቆብ ሁለት ኃይለኞች አስማተኞችን እንዳሳመነ በገድለ ሐዋርያት የተጻፈ ታሪክ አለ ። ሁለቱ አስማተኞች ፊሊጦስና ሄርሞጌኒስ ይባላሉ ። ፊሊጦስ በመጀመሪያ በያዕቆብ ስብከት አመነ ። እምነቱንም ለጓደኛው ለሄርሞጌኒስ ነገረው ። ሄርሞጌኒስም በምትሐት ፊሊጦስን እጅና እግሩን አሰረው ። በዚህም ጊዜ ፊሊጦስ ክርስቲያን በመሆኑ ምክንያት የደረሰበትን አሳዛኝ ሁኔታ ሁሉ ለያዕቆብ በመልእክት አሳወቀው ። ያዕቆብን አስረው እንዲያመጡለት ሰይጣናትን ላካቸው ። ነገር ግን ሰይጣናት በያዕቆብ ላይ አንዳችም ኃይል አላገኙም ። ይልቁንም ሄርሞጌኒስን እንዲያስሩት ያዕቆብ በተአምራት መልሶ ላካቸው ። እንደገናም ፊሊጦስ ሄዶ ሄርሞጊኒስን ከሰይጣን እስራት በክርስቶስ ኃይል እንዲፈታው አደረገ። ቀጥሎም" እኛ ከፋን በከፋ ስለማንቃወም በሰይጣናት እየተሲቃየህ እንዳትኖር ክርስቶስ ምሕረትን ለምንንልህ ል።" በማለት ያዕቆብ ለሄርሞጌኒስ ነገረው ። በዚህም ጊዜ አስማተኛው ሄርሞጌኒስ የክርስቲያኖችን ኃይል ርኅራኄና ቸርነት ተረዳ ። ወደቤቱም ሄዶ የጥንቆላ መሣሪያውን ሁሉ በእሳት አቃጠለ ። ወደ ያዕቆብም ተመልሶ ይቅርታ ጠየቀ በጌታም አመነ እስከመጨረሻም

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ከመንበር ወደ መስቀል

የሰው ፍቅር ከመንበሩ የሳበው እግዚአብሔር ወልድ የመስቀል ሞት ሊሞት ፤ የጠፋውን ሰው ሊፈልግና ሊያድን ወደዚህ ዓለም መጣ።“ በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁም ወዶአልና ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና” ዮሐንስ ወንጌል ምራፍ ፫ ቁጥር ፲፮-፲፯ ።

የሰው ፍቅር ስቦት ከመንበር ወደ መስቀል የመጣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በልዩ ልዩ የባርነት ቀንበር ሥርና አገዛዝ ወድቆ ነበረው ዓለም ከዚህ የሚከተለውን አስተማረ “ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ የተወደዳቸውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል።” የሉቃስ ወንጌል ምራፍ ፬.ቁጥር ፲፱-፳ ።

ለብዙ ዘመን በፍዳ ተይዞ የነበረው የአይሁድ ሕዝብ ይህንን አነጋገር በሰማ ጊዜ ከሮም አገዛዝ ነጻ የምንወጣበት ጊዜ ደረሰ በማለት ክርስቶስን በብዛት ይከተለው ጀመር ። ይህም ሊሆን የቻለው ቀደም ብሎ የአይሁድን ሕዝብ ነፃ የሚያወጣ ሐይለኛ ገገር ይነሣል ። የሚል ትንቢት ተነግር ስለነበር ነው ።

ይህ ትንቢት የተፈጸመ ስለመሰለውም ሕዝቡ ደስተኛ ሊሆን ቻለ ። ነገሩ በዚህ ላይ እንዳለ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በሚመላለስበት ዘመን የአይሁድ ኅብረተሰብ በሙሉ በሮማ አገዛዝ ቀንበር ሥር ወድቀው ጧትም ወዮ’፣ ቀንም ወዮ ፡ ሌሊትም ወዮ እያሉ የሚጮሁ ሕዝቦች ነበሩ ።

ስለዚህም ከአስከፊው የሮማ አገዛዝ ሥር ነጻ ሊያወጣን የሚችለው ባለብዙ ሠራዊት ነው ብለው ያምኑ ነበር ።በመጨረሻም በዳዊት ዙፋን በኢየሩሳሌም የሚነግሥና ከቤተ መንግሥቱ ለሕዝበ እሥራኤል በረከትን የሚሰጥ እንደሚሆን በተስፋ ይጠባበቁ ነበር ።

ከመንበር ወደ መስቀል የመጣ የሰው ፍቅር ስቦት በመሆኑ ፍጹም ፍቅርና ትሕትና በተሞላበት አስተያየት በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ አንዲቷን ሳምራዊት ውኃ አጠጪኝ በማለትና የግል ሕይወቷን የሚነካ ትምህርት በማስተማር ከኃጢአት ወደ ዘላለም ሕይወት መለሳት ። ከዚያም አልፎ ሦስት ቀናት በሰማርያ እየተዘዋወረ ሲጎበኝ ሲያስተምርና፡ አብሮ ሲጸልዩ ሰነበተ። ይህንን የተመለከተ የአይሁድ ሕብረተሰብ በዳዊት መንበር ላይ ነግሦ ሁሉን በእኩልነት የሚገዛና ከሮማውያን ቅኝ ግዛት ተዋግቶ የሚያወጣን እሱ ነው ሲል አመነው ።

ሐያል የሆነው እግዚአብሔር ወልድ ግን የሰው ፍቅር አገብሮት ከሰማያዊ መንበሩ ወደ መስቀል የመጣው ፡የአይሁድ ሕብረተሰብ እንደሚለው ተዋግቶ ከሮም መንግሥት ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣትና በዳዊት ዙፋን ነግሦ ሰዎችን በሥጋ ለመግዛት የመጣ ሳይሆን ፣ በሰይጣን ቁራኛ የተያዘውንና በኃጢአት ሥር ወድቆ የነበረውን ዓለም በመስቀሉና በሞቱ ነጻ ለማውጣት የመጣ መሆኑን ለተከታዮቹ እንዲህ ሲል ገለጸላቸው ። “ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራን እንዲሚቀበል ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር ጴጥሮስም ጌታ ሆይ ይህ ሁሉ አይደርስብህም አለው ጌታም የጴጥሮስ ንግግር ለአላማው እንቅፋት ስለሆነበት ገሰጸው ። “የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፮. ከቁ. ፳፩ - ፳፪ ።

ጌታም ጴጥሮስን የገሰጸበት ዋና ምክንያት ከመንበር ወደ መስቀል የመጣበት ዋናው አላማ የጠፋውን ለመፈለግና ለማዳን ነው ። ይህም በተግባር የሚፈጸመው ከላይ እንደተነገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ መከራ ተቀብሎ ተሰቅሎና ሞቶ በሦስተኛው ቀን ተነስቶ ሕይወቱን መስዋዕት አድርጎ ለዓለም ካላቀረበ በቀር ዓለም እንደማይድን ስለሚያውቅ ነው ጌታቻን ኢየሱስ ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ተናገረው መከራው የሚፈጸምበት ጊዜ ደረሰ ።


“ሰይፍና ጉመድ ይዘው ብዙ ጭፍሮች ወደሱ መጡ ያዙትም እነሆ ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ ጆሮውን ቆረጠው ። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ ሰይፍ የሚያነሱ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ አፍወቱ መልስ ። ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፎሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይችል ይመስልሃል ?አለ የማቴዎስ ወንጌል ምራፍ ፳፮ ከቁጥር ፶-፶፫ ።

ኃያል የሆነው እግዚአብሔር ወልድ የሰው ፍቅር አገብሮት ከመንበር ወደ መስቀል የመጣው መልካም እረኛ ስለ በጎቹ ሕይወቱን ይሰጣል በተባለው መሠረት በራሱ ሞት በራሱ መስዋዕትነት ዓለምን ለማዳን የመጣ መሆኑን ለማስረዳት በመሆኑ ሌሎች እንዲዋጉለት አልፈለገም ።

በተጨማሪም “ የሚሰቀልበትን መስቀል ተሸክሞ በሚጓዝበት ወቅት መስቅሉ ከብዶት ወደቀ መከራ የሚያጸኑበትም ሰዎች ከገጠር ለሚመጣው ለስምዖን መስቀሉን አሸከሙት እሱም ሊሸከመው አልቻለም ። የዓለምን ኃጢአት ለመሸከም የመጣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ያንን ከባድ የመስቀል ሞት እንደገና ተሸክሞ በፍኖተ መስቀል ተጓዘ ። ይህ ሁሉ ግፍና መከራ በሚፈጸምበት ወቅት ዋይ ዋይ የሚሉ ሙሾ የሚአወጡ ሴቶች እንዲሁም እጅግ ብዙ ሕዝብ ሲከተሉት በአየ ጊዜ ኢየሱስ ወደነሱ ዞር ብሎ ለኔ አታልቅሱ ለራሳችሁ አልቅሱ” አላቸው ።

ይህንንም ያለበት ዋናው ምክንያት እሱ ካልሞተና መስዋዕት ሆኖ ካልቀረበ ዓለም ከኃጢአቱና ከበደሉ ሊድን እንደማይችል ሲገልጽላቸው ነው ። በተጨማሪም ወደፊት በኢየሩሳሌም ላይ የሚፈጸመው መከራ ከባድ መሆኑን ሲያብራራላቸው ነው በመጨረሻም ለተራበው ዓለም የሕይወት እንጀራ ለመሆን በመስቀል ላይ ተሰቀለ ። ብዙ መከራም ተቀበለ ።





በዚያም ሰቀሉት ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስን በመካከላቸው ሰቀሉ ።ዮሐንስ ም/ ፲፱ ቁ/ ፲፰

ዮሐንስ አፈወርቅም በክርስቶስ ላይ ስለተፈጸመው ስለዚህ መከራ በጻፈው ቅዳሴ ላይ እንዲህ ብሏል“ ሊቃነ መላእክት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚቆሙለትን በአደባባይ አቆሙት ለሱራፌል አክሊል ያቀዳጀቻቸውን የሾህ አክሊልን ደፋበት ። አዳምን የፈጠሩት እጆች በቅንዋተ መስቀል ተቸነከሩ ።በገነት የተመላለሱ እግሮች በቅንዋተ መስቀል ተቸነከሩ በአዳም ላይ የሕይወት እስትንፋስን እፍ ያለ አፍ ሐሞት የተደባለቀበትን ከርቤ ጠጣ ። ሞትን ለመሻር ፣ ሙታንንም ያድን ዘንድ የማይሞተው አምላክ ሞተ ሲል ተናግሯል ። የዮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ ቁጥር ፵፭-፶፰ ።

አባ ሕርያቆስም በጻፈው ቅዳሴ ማርያም “ ሐያል የሆነውን እግዚአብሔር ወልድን የሰው ፍቅር ከመንበሩ ሳበው። እስከ ሞትም አደረሰው ” ካለ በኋላ ስለ ፍቅር ሲል የፈጸመውን መከራ ሲያብራራ “ቀንድ እያለው እንደ ማይዋጋ ሲያርዱት አንገቱን እንደሚያዘነብል መልካም ከብት ጠላቶች ሲስቡት በፍቅር በኋላቸው የሚከተል ፡ ጸጉሩን ሲሸልቱት እንደማይናገር በግ አፉን አልከፈተም” ሲል ለጠላቶች ያሳየውን ጥሩ ምሳሌነት ገልጾአል ።

እንዳለውም አሮጌ የነበረውን የበግና የላም መስዋዕት ሽሮ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ የመጣው እውነተኛ በግ እንደመሆኑ መጠን የኃጢአትና የበደል መስዋዕት ለመሆን እራሱን በመስቀል ላይ አቀረበ ። ስለዓለምም ኃጢአት እራሱን በፍቃዱ ስዋ ከመንበር ወደ መስቀል የመጣበት አላማው ይህ ነው

ከላይ በርእሱ እንደተናገርነው አይሁድ የመሰላቸው ክርስቶስ በዳዊት ዙፋን ላይ ነግሶ ሲገዛ የሚኖርና በመጨረሻም ከዙፋኑ ላይ እያለ የሚሞት መስሎአቸው ነበረ ። ከመንበር ወደ መስቀል የመጣው ክርስቶስ ግን በዳዊት ዙፋን ላይ ነግሦ ሕይወቱ ያለፈች ሳይሆን ስለበደላችን ስለመተላለፉችን ሮማውያን ባዘጋጁት መስቀል ላይ ራሱን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርጎ የሰጠ ነው ። እንደ አይሁዶች ሐሳብና ምኞት ከመቃብያን አንዱ ሳይሆን ስለ መተላለፋችን ሲተፉበት ፡የእሾህ አክሊል ሲደፉበት ፤ የራሱን ልብስ ገፈው ከለሜዳ ሲያለብሱት ፡ ለበጎው ሥራው ወደ ሞት ሲጎትቱት ፤ በትዕግሥት የተመለከተው መስቀል ላይ ሊቸነክሩት ስለ በደላቸው አባት ሆይ የሚሠሩትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው” እያለ የጸለየ ነው ።

እንደ አይሁዶች ግምት ይህ ሁሉ መከራ ሲወርድበት ዝም በማለቱ በትዕግሥት በመቀበሉ ደካማነትን የገለጸ ቢመስላቸውም የኃያላን ኃያል ቁጣው የራቀ ፡ ምሕረቱ የበዛ መሆኑን በተለይ የመከራ ቀን በሆነው በዕለተ አርብ ታይቷል።

ይህንን ሁሉ መከራ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት ከተቀበለ በኋላ “ሁሉ ተፈጸመ” በሚለው አምላካዊ ቃሉ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለይቶ በመስቀል ላይ ሞተ ክርስቶስ በአይሁድ ከመያዙና ከመሞቱ አስቀድሞ ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት ተላልፎ እንደሚሞትና በሦስተኛውም ቀን እንደሚነሣ ይናገር ነበር ። ይህንን ይሰሙ የነበሩት አይሁዶች ነገሩ ስላሰጋቸው የኢየሱስን አስከሬን ከተሰቀለበት መስቀል ካወረዱ በኋላ ቀበሩት ። መቃብሩን በማሕተም አተሙት ከ፰ የሚበልጡ ዘበኞችም መቃብሩን እንዲጠብቁ አደረጉ ።

ምንም እንኳን ስለኛ ኃጢአት ቤዛ ሊሆነን የኛን ደካማ ሥጋ ቢዋሐድና መቃብሩ ቢጠበቅም የኃያላን ኃያል የሆነ ፍጹም ሰውና አምላክ ነውና በሞተ በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ ። ለምሳሌ በዓለም ብዙ አዋቂዎች ተነስተው በእውቀታቸው በትምህርታቸውና በፍልስፍናቸው ሰዎችን ቢጠቅሙና ታሪካቸው ፡ ሥራቸው በዓለም ቢታወቅም ከሞቱ በኋላ አልተነሱም ። ክርስቶስ ግን ከሞት እንደተነሣ አያሌ ምስክሮች አሉት ።

፩ኛ/ ክርስቶስ በተነሣ ጊዜ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆኗል ። መቃብሩን የሚጠብቁትም ጭፍሮች ደንግጠው እንደሞቱም ከመሆናቸውም በላይ በኋላ ወደ ከተማ ወጥተው የሆነውን መስከረዋል ። የማቴዎስ ወንጌል ም.፳፰ ፩-፲፭ ።

፪ኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበረበት መቃብር ባዶውን መገኘቱና የተከፈነበትም የከፈን ጨርቅ ከመቃብሩ ውጭ ተጠቅሎ መገኘቱ የክርስቶስን መነሣት ያረጋግጣል ።

፫ኛ/ ዋናውና የመጨረሻው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ተገኝቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምሣ መጋበዙ ነው ። ይህም ከሙታን ለመነሳቱ በቂ ምስክር ነው ።

እንግዲህ ስለኛ ኃጢአት የሞተውና የተነሣው አምላክ በረከትን ፣ ሰላምን፡ ልጅነትን ሊሰጠን ጠዋት ማታ ይጠራናል ። ይህንንም ለመቀበል መስቀሉን ተሸክመን ፤ ስለትንሣኤው እንመስክር ከመንበር ወደ መስቀል የመጣው ለኛ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

## ጾም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ....

ከገጽ ፰ የዞረ

በተባለው ድርሰቱ ዘምሯል ። ቤተ ክርስቲያንም ሰዓታትና ማኅሌት በመቆም የቅዳሴ ሥርዓት በማከናወን ታስበዋለች ።

ቀደም ብሎ እንደተገለጸውም እንደሌሎች ሳምንት መታሰቢያነቱ የኒቆዲሞስ ሳምንት ይባላል በተለይ ከሰኞ እስከ ረቡዕ የሚዘምሩት ዜማዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚያደሉት ወደአራራይ ነው ።

ይህም የሚያመለክተው የጾመ ድጓ ቁመት ፍጻሜ መቃረቡን ሲሆን በሌላ ትርጉምም አራራይ ዜማ የሚመስለው በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያስረዳል ምክንያቱም ለማንኛውም ሥራ ፍጻሜው እርሱነውና ።

ከዚህም ሌላ ከረቡዕ ጀምሮ ተጽኢኖ ወይም አርእሳተ ምህላ ይኖራል ። በተለይ ዓርብ "ተጽኢኖ" ተብሎ ይጠራል ። በዚህ ዕለትም ዳዊቱን በመላ በማስተዛዘል የተለየ ሥርዓት ሲካሄድ ይውላል ።

በመጨረሻም ጌታ ኢየሱስ "በአህያ ውርንጭላ ላይ ሆኖ ወደኢየሩሳሌም በሰላም ገባ" የሚለው ሰላም በከበሮና ጸናጽል ጭምር ይዘመራል በዚህ ቀን ተዘግቶ የነበረው የከበሮና የጸናጽል ድምፅ ይከፈታል ። በሚቀጥለው ቅዳሜና እሑድ ሥነ ሥርዓትም እንደመጣቢያ ሆኖ ይቀጠራል ምክንያቱም የሚዘመረው መዝሙር እምብዛም አይራራቅምና ነው ።

፪ኛው እሑድ ሆሣዕና ሲሆን ከሰዓት በኋላ ጀምሮ ዋዜማ ይቆማል ። የቅዱስ ያሬድ ዜማም በዝማሜ በከበሮና ጸናጽል ይካሔዳል ። በተለይ በታላላቅ አድባራት የእሑድ ቁመት ከሌሊቱ ፩ ሰዓት ጀምሮ እንደሌሎች በዓላት ስቡሕ ወውዱስ ተብሎ ይጀመራል ።

የዚህ በዓል ዓላማ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ "ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት" እያሉ ሕፃናት ሽማግሌዎች ዘንባባ ይዘው በክብር እንደተቀበሉት የሚገልጽ ነው ።

የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት በምሥራቅና በምዕራብ ፣ በሰሜንና በደቡብ ካህናቱና ምእመናኑ ጭምር በአራቱ ማዕዘን እየዞሩ የሚቀጥለውን ሰሙነ ሕማማት በማስታወስ ግብረ ሕማማት ይነበባል የተለያዩ የቅዱስ ያሬድ ዜማዎች ይዜማሉ ።


የቅዳሴው ሥርዓት ከተከናወነ በኋላም የተሰበሰበውን ሕዝበ ክርስቲያን "እግዚአብሔር ይፍታሕ በማለት ታሰናብታለች ምክንያቱም ሰው ቢሞት እስከሚቀጥለው ዓርብ ስቅለት ድረስ በቤተ ክርስቲያን መምሪያ መሠረት ጸሎተ ፍትሐት ፣ አይደረግምና ነው ከሆሣዕና ሰኞ ጀምሮ እስከ ስቅለት ድረስ የሕማማት ሳምንት ይባላል ይህም የክርስቶስን ጸዋትወ መከራ በማሰብ ግብረ ሕማሙንና የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ ፣ ከዚያም ጋር የቅዱስ ያሬድን ድርሰትና ዜማ ጣልቃ በማስገባት ሥርዓቱ በሚያዘው መሠረት ይዘመራል ።

ከዚህ ሌላ ግን የጸሎተ ሐሙስን የስቅለትንና የቀዳሚት ሥዑርን ሥርዓቶች ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ስለሚከታተሏቸው ከማቅረብ ተቆጥበናል ።

ስለዚህ ለክርስቲያኖች ጾም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ሥርዓት ለማቅረብ ያስፈለገው ምክንያት ካህናቱ ሌሊት በሰዓታት ፣ ቀን በቁመት ከዚያም በመጨረሻ የቅዳሴ ሥርዓት የሚከናወኑበት ሁላችንንም ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ስለሆነ በጾም ብቻ ሳንወሰን ሥርዓቱንም ጭምር በመጠኑ እንድናውቅ ነው ።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ከእግዚአብሔር ቃል ሳይወጣ ድርሰቱን እንዴት እንዳዘጋጀው ለመጠቆም ስለሆነ የቀረበውን ጽሑፍ ማንበብ ብቻ ሳይሆን በተግባር እንድንተረጉመው ያስፈልጋል ።

ነቅዓ ጥበብ ወንድም





## የአቶ ሙላቱ ኩቾ ዜና ዕረፍትና አጭር የሕይወት ታሪክ

ከሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ

አቶ ሙላቱ ኩቾ የወርቁ ጉባ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ም/ ሊቀመንበር ፲፱፻፳ ዓ.ም. በወላሞ ሶዶ ሀገር ልዩ ስሙ ቦዲቲ ከተባለው ቀበሌ ከአባታቸው ከአቶ ኩቾ አያና እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ቡፋትኬ ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በደጃዝማች ዳርጌ ት/ቤት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ ፣ ከዚያ ቀጥሎ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. በአራተኛ መድፈኛ ሻለቃ ክፍል በወታደርነት ተቀጠሩ በዚያም እንዳሉ በ፲፱፻፵ ዓ.ም. በጦር ኃይሎች ሆስፒታል በሕክምና ችሎታቸው ተመርጠው የሕክምና ሥራቸውን በጥንካሬ ይሠሩ ጀመር ።

ሚቹ አቶ ሙላቱ ኩቾ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. የሕክምና ምስክር ወረቀትን ተቀብለው የሕክምና ሥራቸው በሚገባ አሟልተው መሥራታቸውን ቀጠሉ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ወ፡ሮ ትሩፋት ገብረ ሃናን በሕግ አግብተው ብዙ ልጆችን አፍርተው ከአዲስ አበባ ወደ ጂማ በሥራ ተዛወሩ በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. በአውራ ጉዳና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በሐረር ክፍለ ሀገር በኡጋዴን ከፍ ያለ አገልግሎትን አበረከቱ በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. በሸዋ ክፍለ ሀገር በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ በወቀት ወረዳ ልዩ ስሙ ዙጢ ከተባለው ቀበሌ ላይ በተቋቋመው አውራ ጉዳና መሥሪያ ቤት እስከ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ከፍ ያለ የሕክምና አገልግሎት አበረከቱ ለሀገራቸው በታማኝነት ከመሥራትና ከሚኖሩበትም አካባቢ ቤተ ክርስቲያንን ከማገልገል ወደኋላ የማይሉ ታላቅ ሰው ነበሩ ።

አቶ ሙላቱ ኩቾ ፲፱፻፸ ዓ.ም. ከላይ ከተጠቀሰው መሥሪያ ቤት በሰላም ተሰናብተው አሁን ሕይወታቸው ካለፈበት ቀበሌ ቤት ሠርተው የአራት ጉሳ



አቶ ሙላቱ ኩቾ እኚህ ነበሩ

ሕዝብ የሚገኝበትን የአካባቢያቸውን ሕዝብ ሲያክሙ ደሃውን በነፃ ገንዘብ ሳያስከፍሉ ከሀብታሙም ቢሆን መጠነኛ ገንዘብ እንጂ ብዙ ገንዘብ ሳይጠይቁ አገልግሎታቸውን በሚገባ አበርክተዋል ።

አቶ ሙላቱ መንፈሳዊ ስሜትስ ለነበራቸው የክርስቶስ ቃል እንዲስፋፋ ክርስቲያኖችም በክርስትና እምነታቸው እንዲጠናከሩ በልዩ ልዩ መንገድ ይጥሩ ነበር ። ስለዚህ የአካባቢውን ሕዝበ ክርስቲያን ለመርዳት ሲሉ ወርቁ ጉባ ከተባለው ቀበሌ የቅዱስ ገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን ለማስተከል ብዙ ደክመዋል ። ከብዙ ድካም በኋላ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ መስከረም አንድ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያኑን የመሠረት ድንጊያ አስቀምጠው ግምቱ ከ፷ሺህ ብር በላይ የሆነ ቤተ ክርስቲያንን አሠርተው የቅዱስ ገብርኤልና የቅድስት ማርያም ጽላቶችን አስገብተው ሲያበቁ አስፈላጊዎች የሆኑትን ንዋያተ ቅዱሳትም በግል ገንዘባቸው አሟልተው አሁን አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው አቶ ሙላቱ ኩቾ በ፶፰ ዓመት ዕድሜያቸው ጥር ፳፫ ለ፳፬ ቀን አጥቢያ ከሌሊቱ በግምት ፮ ሰዓት ተኩል መዝጊያውን ማን እንደከፈተው ሳይታወቅ ከመኝታ ቤታቸው ተጎትተው ወደ ውጭ ከተወሰዱ በኋላ ከቤታቸው በረንዳ ላይ በጥይት ተደብድበው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

አቶ ሙላቱ ሥጋችሁን የሚገሉትን አትፍሯቸው ነፍሳችሁን ለመግደል ሥልጣን ያለውን ፍሩ እንጂ ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል በመከተል እግዚአብሔርን በመፍራት መንፈሳዊ ተግባርን በሚገባ አከናውነው ሰማዕትነትን ተቀብለዋል የአቶ ሙላቱ ደም እንደ አቤልና እንደዘካርያስ እንደ ጳውሎስና እንደጴጥሮስ ደም ሆና የክርስቶስ አማኞችን የምታበዛ እንጂ የምታስደነግጥና የምታስፈራ መሆን አይኖርባትም ፣ በክርስቶስ አምነው መልካም ሥራ ሠርተው ያለፉ ሁሉ ሞታቸው ሕይወታቸው ነውና ።

ቤተ ክርስቲያናችንም ለአቶ ሙላቱ ኩቾ የምትሰጠው ምስክርነት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለናትናኤል ከሰጠው ምስክርነት ያልተለየ ነው ስለእርሱም ሲመሰክር ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ እንዳለ የእኛም ቤተ ክርስቲያን እነሆ በእውነት አቶ ሙላቱ ተንኮል የሌለባቸው የክርስቶስ ቤተ ሰብእ ናቸው ብላ ትመሰክራለች ዮሐ ፩. ፵፯ - ፵፱

አቶ ሙላቱ የብዙ ሕፃናት አባት የብዙ ሕሙማን ሐኪም ነበሩ ቢሆንም መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ ተብሎ ለአዳም በተነገረው ቃል መሠረት የማይቀረውን የሞት ጽዋ በሚያሰቅቅና በሚዘገንን ሁኔታ ተቀብለዋል ።

ሞታቸው እንደተሰማ ወዲያውኑ ካህናቱ ተሰብስበው ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱ አድረው ሲነጋ ደግሞ የአድባራትና የገዳማት ካህናት የጸሎተ ፍትሐቱ



www.ethiopianorthodox.org

ተካፋዮች ሆነው ውለዋል በዙሪያቸ ውና በአካባቢያቸው የሚኖረውም ሕዝ ብ መሪር የሆነ ኃዘኑን በልዩ ልዩ መንገድ ሲገልጥ ውሏል በልቅሶውም ዕለት ብዙ ቅኔዎች ተደርሰዋል ፤ ከብዙዎችም ቅኔዎች አንዱ የሚከተለው ነው ።

ሥላሴ ቅኔ ዘአሊቃ ሐዋዝ

በፀደይ ወበመጸው ፤ ከልኤሆሙ ሞት ወመቃብር ፤ ነትገብነ ምልዓቱ ለወልደ

አማኑኤል ማይ እስመ ጸንአ በጊዜ ምልአቱ ግብተ ሞት ሀጋይ

እስከነ ይየብስ ወልድ ፍሬሁ ለአማኑ

ኤል ስርናይ

ወይቤ ገብርኤል ቃለ ነቢይ

ወልደ አማኑኤል አንተ ዘሀገር ዐሐይ

በሞትከ በከየት ሰማይ

ወደ አማርኛ ሲተረጐም

በሁለቱም ፀደይና መጸው ሞትና መቃብር ጊዜ ወልደ አማኑኤል ውኃ ከሙላቱ ጐደለብን (ወልደ አማኑኤል የሟቹ ስም ነው ።)

በመሙሊያው ወቅት ድንገተኛ ሞት በጋ ጸንቷልና የወልደ አማኑኤል ስንዴ ፍሬ እስከሚደርቅ ድረስ የነቢይ ቃል ገብርኤልም ወልደ አማኑኤል የሀገር ፀሐይ ነህና ማለት ነው አንተ በሞትህ ጊዜ እንኳን ሰው ሰማይ ሳትቀር አለቀሰች ማለት ነው ሞት ለሁሉም በየተራ የሚደርስ በመሆኑና ሰውም ሁሉ በሞት የሚጠራበት መንገድ የተለያየ በመሆኑ አቶ ሙላቱ በድንገተኛና ባልተጠረጠረ ጊዜ ቢሞቱም የሚሄዱት ወደ ፈጣሪያቸው ስለሆነ ለዕርሳቸው ዕረፍተ ነፍስን ለቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትን እን ዲሰጣቸው የዘወትር ጸሎታችን ነው ።

# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

### ሥርዓተ አንቀጽ

ደራሲው ወይም ተናጋሪው መጠነኛ ስፋት ያለውን አንድ ፍሬ ሐሳብ የተሸከመ ኃይለ ቃል ያለበትን የአንድ ሥረ ወጥ ጽሑፍ/ አርቲክል/ ንዑስ ክፍል በ አንድ ዐረፍተ ነገር መግለጥ ካልተቻለ ው በቀር በአንቀጽ መለየት ወይም መከፋፈል ይኖርበታል።አንቀጽ ማለትም ተዛማጆች የሆኑ ጥቂት ዐረፍተ ነገሮች ተረዳድተው አንድን ፍሬ ሐሳብ ግልጥ /ብሩህ/ ለማድረግ የሚችሉበት ክፍል ነው ። ይህም በልሣነ እንግልጣር ፓራግራፍ ተብሎ የሚጠራው ነው ።

አንቀጽ ወይም ፓራግራፍ ሁል ጊዜ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ መጀመር አለበት። ከዚህም በተረፈ ዐረፍተ ነገሮችም ሆኑ አንቀጾች በመርዘም እንዳይውጡአቸ ው አማራጭ የሌለው ዓይነተኛ ዘዴ ቅ ጽሎችን መስተዋድድና መስተፃምር ሐረጎችና የመሳሰሉትንም ነገሮች አለ ማብዛት ነው ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ አያስፈልጉም ለማለት ሳይሆን አ ገባባቸው ሥነ ሥርዓትንና መጠንን የ ተከተለ እንዲሆን ጥንቃቄ ማስፈለጉን ለመጠቆም ያህል ነው ።

የድርሰት አከፋፈል

ጥራትና ውበት ያለው ማንኛውም ድር ሰት ወይም ንግግር በሦስት ይከፈላል ይኸውም

፩- መግቢያ /ኢንትሮዳክሽን
፪- ሐተታ //ቦዲ/
፫- መደምደሚያ /ኮንክሉሽን ይኖሩታል ።

፩- መግቢያ ፡- የአንድ ድርሰትን ወይም የንግግርን ርእስና ዓላማ ከአንባቢዎች ወይም ከአድማጮች ጋር ለማስተዋወቅ የምንሞክርበት መቃረቢያ ስለሆነ ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ መነደፍ ይኖርበታል "የሚያጠግብ እንጀራ ከሰበከቱ (ምጣዱ) ይታወቃል" እንዲሉ አንባቢውም ሆነ አድማጩ ወደፊት የሚቀጥለውን የምሉእ ሐተታ ውጤቱን በናፍቆት ወይም በሰቂለ ኅሊና መጠባበቅ የሚችለው ገና ከመግቢያው በሚገኘው የብሩህ ተስፋ ሰጭ መግለጫ ጥራትና ውበት ነው ።

፪- ሐተታ ፡- ዋናው የድርሰት ባሕረ ሐሳብ ድርሰቱ ተነብቦም ሆነ ተነግሮ ባጠቃላይ ቅርፅና ይዘቱ ጥቅምና ጉዳቱ ገለባና ምርቱ ተለይቶ ደራሲውን ከማመስገንም ሆነ ከመንቀፍ ደረጃ ወይም ከወሣኝ ነጥብ ላይ የሚያደርሰው ይኸው ክፍል ነው ።

፫- መደምደሚያ፡- የተጻፈው ድርሰትም ሆነ ንግግር /ቃል ድስኩር/ ተመዛዝኖ ፍሬ ነገሩ ተጨምቆ የነጠረ ማጠቃለያ ዝክረ ነገር ትቶ ለማለፍ የሚያስችል መሰናበቻ ስለሆነ አጻጻፉ ብርቱ ጥንቃቄን ይጠይቃል ። ይህም የመደምደሚያ ሐሳብ በአንባቢዎች ወይም በአድማጮች አእምሮ በማይረሳ ሁኔታ ተቀምጦ እንዲኖር ማድረግ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል ።

ዳሩ ግን በቀጥታ የክለሳ ዓይነት መሆን የለበትም።ዋና ዋናዎቹን ነጥቦች ብቻ በአጭር አስተዋጽኦ መልክ ብጥርጥር አድርጐ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ይህም ማለት ውበት ባለው አገላለጥ ፍሬ ነገሮችን በትክክል ለማስጨበጥ እንጂ ደጊመ ቃል እንዲበዛበት አያስፈልግም ። ለዚህም አብነት መሆን የሚችለው ማስረጃ የረጅም ዘመን የድርሰት አጻጻፍ የንግግር ጥበብ ልምድ ያላቸው ደራሲያን መጻሕፍት በጥንቃቄ አንብቦ የመግቢያ የሐተታና የመደምደሚያ አቀራረብ ዘዴያቸውን መርምሮ ዐሠረ ፍኖታቸውን (ዱካቸውን) ለመከተል እንጂ መመሪያ በመንደፍ ብቻ የሚወሠን አይደለም ።



# ታላቁ ያዕቆብ

ከገጽ ፲፩ የዞረ

በክርስትና እምነቱ ጸንቶ ኖረ/የሐዋር ያት ታሪክ ዘአባዲያስ ፩፡፩-፱/

ይህን የመሰለ ታሪክ በሐዋ.፲፱፡፲፬-፲፱ ተጽፎ ይገኛል ። ስለዚህ ታላቁ ያዕቆብ በሁለቱ አስማተኞች ላይ ያሳየው ተአምራዊ ታሪክ ሊታመን የሚገባው ነው ። ዛሬም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያል ተለያቸው የቤተ ክርስቲያን ሰዎች እን ደ ሐዋርያት በሰይጣናትና በአስማተኞ ች ላይ ኃይልና ሥልጣን አላቸው ።ርኩሳን መናፍስትን ለሐዋርያት ሥልጣን የሰጠ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬ እ ስከዘለዓለምም ያው ነውና ።

ፊሊጦስና ሄርሞጌኒስ የተባሉት አስ ማተኞች በ፪ኛው ጢሞቴዎስ ፩፡፲፭ ላይ የተጠቀሱት የጳውሎስ ተቃዋሚዎች የነበሩት እንደሆኑ የሚተርኩ ሊቃውን ት አሉ ። ነገር ግን ይህ አስተያየት ትክክል አይመስልም ምክንያቱም ጳውሎ ስ የጢሞቲዎስን መልእክት በሚጽፍ በት ጊዜ ያዕቆብ ሞቶአል ።

ታላቁ ያዕቆብ በአሁኑ ጊዜ የእስፔይ ን ተራዳኢ ቅዱስ እየተባለ ይጠራል ። ይህም የተባለበት ምክንያት በትውፊት እንደሚነገረው ቅዱስ ያዕቆብ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ ወደ እስፔይን ሄዶ ወንጌልን አስተምሮአል ። ከዚያም ተመልሶ በኢየሩሳሌም ሳለ ሄሮድስ በ ሰይፍ አስገደለው ። ይህም የሆነው በ፵፬ ዓ.ም. ነበር ። ያዕቆብ ከሞተ በኋላ ፊሊጦስና ሄሮሜጌኒስ አስከሬኑን ይዘው በ ኢዮጴ በኩል በመርከብ ተሳፍረው ሲሄዱ እስፔይን ወደብ ደረሱ ። ከዚያም ዛሬ ኤል ፓድሮን ተብላ በምትጠራው ፍላቪያ በተባለች ቦታ ሬሣውን አ ኖሩት ።

በ፰ኛው ምእት ዓመት አረመኔዎች እስፔይንን በወረሩ ጊዜ የያዕቆብ አስከ ሬን ከጠፋ በኋላ በ፱ኛው ምእት ስለተ ገኘ ንጉሥ አልፎንስ ወስዶ ኮምፓስቴ ላ በተባለች ቦታ አስቀመጠው ። እስካ ሁንም ኮምፓስቴላ የያዕቆብ ዐፅም እን ዳለበት ስለሚታመን ብዙዎች ተሳላሚ ዎች ወደ እርስዋ በየጊዜው ይጓዛሉ ።

ካምፓስታላ ማለትም ያዕቆብ አፓስት ል/ ያዕቆብ ሐዋርያ/ ማለት ነው ይላሉ።

ቅዱስ ያዕቆብ በምዕራብ ቤተ ክርስ ቲያን እንደ አውሮፓ የቀን አቆጣጠር ሐምሌ ሦስት ቀን ይከበራል በኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን እንደ ኢት ዮጵያ የቀን አቆጣጠር ሚያዝያ ፲፯ቀን በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ይከ በራል ። በዚሁ ዕለት ምእመናን በአማ ላጅነትና በሐዋርያዊ ቅድስናው ይማ ፀናሉ ። ሐዋርያው ያዕቆብ ዓሣን ከማ ጥመድ ይልቅ ሰዎችን በክርስቶስ ፍቅ ር እንዲስብ ፋብሀሀ ግሠቶዕ ዛሬም ሰዎች ሁሉ ወደ ክርስቶስ በእምነት እን ዲቀርቡ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲ ገቡ ይማለዳል።ቅዱስ ያዕቆብ ከሐዋርያ ት ሁሉ በፊት በሰማዕትነት በመሞቱ ለ መጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ኃይልና ድልን አስገኝቶላታል ። ለዛሬዋ ሐዋር ያዊት ቤተ ክርስቲያንም የዚህ ሰማዕት ና ሐዋርያ ትምህርት በሐዋርያት መሠረተ እምነትቆራጥነትና እውነተ ኞነት ለዘለዓለም ጸንታ እንድትኖር ኃይልና ግርማን ይሰጣታል ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ቃላት

ሞት ለዘለዓለም በመሸነፍ ባሕር ይዋጣል እግዚአብሔር አምላክ ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል ፤ የሕዝቡንም ስድብ ከመድር ሁሉ ይሽራል እግዚአብሔር ተናግሯልና ፤ በዚያም ቀን ይባላል እነሆ ይህ አምላካችን ነው ተስፋ ያደረግን ው ያድነንማል ይህ እግዚአብሔር ነው ደጅ እየፀናን በተስፋ የቆየነው ። በማዳኑ ደስ ይበለን ሐሴትም እናደርግ ትን. ኢሳ. ም. ፳፭ ቁ ፰

ከሲኦል እጅ አድናችኋለሁ ከሞትም እበጀችኋለሁ ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት ነው ? የሞት መውጊያው ኃጢአት ነው ። የኃጢአትም ኃይል ኦሪት ነው ። ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ። ትን.ሆሴዕ.፲፫. ቆሮ ፲፭.፲

ክርስቶስ ደ[illegible] እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ አመፀኞች አንድ ጊዜ በ[illegible]ት ምክንያት ሞቷልና ፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስግን ሕያው ነው በእርሱም ደግሞ ሂዶ በወሕኒ ቤት ለነበሩ ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው ፩ኛ/ ጴጥሮስ ፫.፲፰ ።

በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን እንግዲህ በነጻነታችሁ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ ገላ.፭.፩ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ከመስማት ጋር ማየት

በጅቡቲ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን
ያት (ምእመናን) ናት ) በጅቡቲ ቤተ ክ
ርስቲያን እንዲሠራላቸው ለኢትዮጵያ
ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ካቀረቡ ዘ
መናት አልፈዋል ፣ ይሁን እንጂ ምእመ
ናኑ አሁንም ተስፋ ሳይቆርጡ ባቀረቡ
ት ጥያቄ መሠረት ቤተ ክርስቲያኑ ከ
መሠራቱ አስቀድሞ ጳጳስ እንዲሾምላ
ቸው ከቅዱስ ፓትርያርኩ ተፈቅዶ ጳጳ
ሱ ሥራቸውን ጀምረዋል ።

በጅቡቲ ስለሚሠራው ቤተ ክርስቲ
ያንና ስለምእመናኑ አንድነት በተደጋ
ገመ ጊዜ በጋዜጦችና በመጽሔቶች ሪ
ፖርት እየቀረበ ዝርዝር ሁኔታውን ሰም
ተናል ።

ከምእመናኑ ፣ ከአንዳንድ በጐ አድራጊ
ዎች ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚሰበሰበ
ው ገንዘብ እንዳለፈው ጊዜ የትም ባክኖ
እንዳይቀር በቤተ ክርስቲያኑ ስም በጅ
ቡቲ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሒሣብ
ቁጥር ፩፻ ፶፱ ተከፍቶ መጠራቀሙንም
ተረድተናል ።

አዎ ከጆሮ ይልቅ በዓይን ተመልክቶ
ፍሬውን ከግርድ መለየት እንደሚቻል
ሁሉ ከታህሣስ ፳፮ እስከ ጥር ፲፫ ቀን
፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ድረስ በጅቡቲ ተገኝተ
ን በጆሮ የሰማነውን በዓይን ከመመል
ከታችንም ይልቅ ስለቤተ ክርስቲያኑ
መሠረት ስለምእመናኑ አንድነትና ስለ
ገንዘብ አስተዋጽኦ ከምእመናኑ አንዳ
ንዶቹን አነጋግረናል ።

ጥያቄ በጅቡቲ ቤተ ክርስቲያን እንዲ
ሠራላችሁ ጥያቄ ያቀረባችሁት አሁ
ን ነው ወይስ ከዚህ በፊትም ጠይቃች
ኋ ኑሯል?

መልስ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ስንዘጋ
ጅ ኀዘን እየተሰማን ነው ሆኖም ቤተ ክ
ርስቲያን እንዲሠራልን ጥያቄ ያቀረብ
ነው አሁን ብቻ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ
ነው ነገር ግን ጥያቄአችን ጆሮ ዳባ ልበ
ስ ተብሎ ከመታለፉ በስተቀር ለጥያቄ
አችን መፍትሔ አላገኘንም ያሳዘነንም
ይህ ሁኔታ ነበር ።

ጥያቄ ለመሆኑ በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስ
ቲያኑን ለማሠራት በቂ ገንዘብ ሰብስባ
ችሁ ነበር?

መልስ አዎ የገንዘብ ሰብሳቢ ኮሚቴ በ
ማቋቋም በሕጋዊ መንገድ ከእርዳታ
ሰጭ ክርስቲያናዊ የግላዊ ድርጅቶች ፣
ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከምእ
መናን ገንዘብ ለመሰብሰብ ተችሎ ነበ
ር ።

ጥያቄ ገንዘብ ለመሰብሰብ ከተቻለ ቤተ
ክርስቲያኑ ሊሠራ ያልቻለበት ምክንያ
ት ምን ነበር?

መልስ ሊሠራ ያልቻለበት ምክንያት በ
ክርስትና ሕይወታችን እንደምናምነው
የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ ይመ
ስለናል ፣ ለሥራው አለመቃናት ከነበ
ረው ምክንያት ግን ባቀረብነው ጥያ
ቄ መሠረት ከቤተ ክህነት የተሰጠ ድጋ
ፍ ባለመኖሩ ነው ።

ጥያቄ ወደ አሁኑ እንቅስቃሴአችሁ መ
ለስ በማለት ስለ ቤተ ክርስቲያኑ መሠ
ራት አንዳንድ ነጥቦችን ብትገልጹል
ን?

መልስ ወደ አሁኑ እንቅስቃሴ ስንመለ
ስ እግዚአብሔር አንድን አገር ያለ አን
ድ ጠባቂ አይተዋትም እንደሚባለው እ
ግዚአብሔር ለአብያተ ክርስቲያናት መ
ስፋፋትና መጠናከር ፣ ስለሃይማኖታች
ን እድገት የሚያስቡትን አባት ብፁዕ ወ
ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በረቂቅ
ጥበቡ መረጠልን እኛም ከዚህ በኋላ የ
ተረሳና አስታዋሽ ያጣ ጥያቄአችንን በ
መቀስቀስ ያለምንም መወላወል ጥያቄ
አችን በቅዱስነታቸው ፊት ተቀባይነት
አግኝቶአል በዚህም የሞራል ድጋፍ በ
ማግኘታችን ተደሰትን ።

ጥያቄ እንዳላችሁት ሁሉ ለእግዚአብሔ
ር የሚሳነው ነገር የለምና ቅዱስነታቸ
ውን አስነሳ በመሆኑም ጸሎት ቤት ሳይ
ሠራ ፣ ለቤተክርስቲያኑ ማሠሪያ በቂ ገ
ንዘብ ሳይሰበሰብ በቀጥታ ጳጳስ እንዲ
ሾም የተደረገበት ምክንያት እንዴት
ነው?

መልስ ቀደም አድርገን እግዚአብሔር
አንድን አገር ያለአንድ ጠባቂ አይተዋ
ትም ያልነው ስለዚህ ነው ምክንያቱም
ባለፈው ድካማችን ስንወጣ ስንወርድ
የተመለከቱ የቤተ ክርስቲያን አባቶች
ነበሩ ይሁን እንጂ ለጥያቄአችን ምንም
ዓይነት መፍትሔ እንዳልፈለጉለት ታሪ
ክ እየመሰከረ ነው አሁን ግን ለሁሉም
የድካሙን ዋጋ እንዲያገኝ የሚሹ ቅዱ
ስ አባታችን በመጀመሪያ ቤተ ክር
ስቲያኑ ይሠራ አንድ አጽናኝ ካህን ይላ
ክ የሚል ምክንያት ሳይፈጥሩ በቀጥታ
ጳጳስ እንዲሾም በማድረጋቸው ተደስተ
ናል የቅዱስነታቸው ጸሎትም የቤተ ክ
ርስቲያኑን ሥራ እንደሚያፋጥነው እ
ናምናለን ፕላኑ አልቆ ሥራው ቢጀመ
ር ሳያልቅ እንቅልፍ የሚወስደው ክርስ
ቲያን አይኖርም ፣

ጥያቄ ከመስማት ማየት የታመነ ነው
እንደተባለው ስለ ቤተ ክርስቲያኑ መሠ
ራት ምእመናኑ እንዲተባበሩ በመጠኑ
ም ቢሆን ተመልክተናል ፣ ቦታውም ለ
ቤተ ክርስቲያኑ ማሠሪያ ፣ ለት/ቤትና
ለመንበረ ጵጵስናው ጽ/ቤት እንደሚበ
ቃ ተነግሮ ነበር በዓይን እንዳየነው ከሆ
ነ ግን የብፁዕ አቡነ ኤልያስ ጥረት ባይ
ታከልበት ኑሮ በጣም አነስተኛ እንደነ
በር ግልጽ ነው ይህ ሁኔታስ እንዴት
ነበር ?

መልስ ይህ አባባል ግልጽ ነው እኛ እን
ደምናስበው በዓይን ግምት ለተጠቀሱ
ት አገልግሎት እንደሚቃ እንገምት ነ
በር ነገር ግን በመሐንዲስ ሲጠና አስቸ
ጋሪ ሆኖ በመገኘቱ በብፁዕ አቡነ ኤል
ያስ ጥረት ሊስተካከል ችሎአል ከዚህ
ላይ ጨምረን ልንገልጽ የምንወደው ብ
ፁዕ አቡነ ኤልያስ ተሾመው ወደ ጅቡ
ቲ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ቤተ ክር
ስቲያኑ መሠራትና ስለ ምእመናኑ አን
ድነት የፈጸሙትን መንፈሳዊ ሥራ እግ
ዚአብሔር ይቁጥረው እንጂ ይህ ነው
ብለን ብንዘረዝረው መስመሮች ያንሱ
ናል ፣ ሆኖም አባታዊ ተልእኮአቸው
ፍሬአማ እየሆነ በመሔዱ በተሰጠን ዕ
ድል አምላክን እናመሰግነዋለን ብለ
ዋል ።



እንግዲህ ከምእመናኑ ጠይቀን እን
ደተረዳነውና የዓይን ምስክር በመሆን
እንደተመለከትነው የምእመናኑ ጥያቄ
መልስ ሳያገኝ ለዘመናት መኖሩን ስናረ
ጋግጥ በአሁኑ ጥያቄአቸው ግን የተሟ
ላ መፍትሔ ማግኘታቸውን ተረድተና
ል ።

በዚህም መሠረት በቤተ ክርስቲያኑ
ስም በጅቡቲ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
፩፻ ፶፱ የሒሣብ ቁጥር ተከፍቶ በማንኛ
ውም አቅጣጫ የሚገኘው እርዳታ እን
ደሚጠራቀም ተመልክተናል ይህም ገን
ዘብ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ካልተጀመ
ረ በቀር በማንም ማን ሊንቀሳቀስ እን
ደማይችልም አረጋግጠናል ።

የቦታው ሁኔታና የፕላኑ ጉዳይ በብ
ፁዕ አቡነ ኤልያስ ጥረት ሕጋዊ መንገድ
መያዙ የሚያስደስት ሆኖአል ከምእመ
ናኑ ለቤተ ክርስቲያኑ ማሠሪያ ከፍተኛ
ገንዘብ ያዋጡ ጥቂቶች ናቸው ሆኖም
ሥራው ቢጀመር ወርቃችንንም ቢሆን
ሸጠን ሥራው እንዲጠናቀቅ እናደርጋ
ለን የሚሉትንም አነጋግረናል ።

የፕላኑ ጉዳይም ተጠናቆ የግምቱ ሂ
ሣብ በማለቅ ላይ መሆኑን ከብፁዕነታ
ቸው ዘንድ ጠይቆ ለመረዳት ችለናል
ይህም በቅርብ ጊዜ ሥራው ለጨረታ እ
ንደሚሲጥ ተገልጿል ለማጠቃለል በጅ
ቡቲ የሚሠራው ቤተ ክርስቲያን በቅ
ርብ ጊዜ ተጠናቆ የራሱን አገልግሎት
በራሱ ለመስጠት ሲችል የልዑካኑ ቁጥ
ር ወደ ፭ ከፍ እንደሚል በተስፋ እንጠ
ብቃለን ።

ሊቀካ. በለጠ አበበ

# በኩረ ትንሣኤ (የትንሣኤ መጀመሪያ)

ከፀሐይ በታች ያለ ፍጡር ሁሉ በሞት
ጥላ ሥር ይጋረዳል ። ይሁን እንጂ የሞቱ
ሰዎች ሁሉ ለዘለዓለም እንደሞቱ ይቀ
ራሉ ማለት አይደለም አንድ ቀን ይነ
ሣሉ ። ከሞቱ በኋላም ሕይወት አለና
የሞተ ሰው እንደገና በሕይወት እንደ
ሚነሣም ለማስተዋል የጌታችን የመድ
ኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ
በቂና የማያጠራጥር ፣ ተቀዳሚ የሌለው
ጉልህ የመጀመሪያ ማስረጃ ነው ስለዚ
ህም የክርስቶስ ትንሣኤ በትንሣኤ ዘጉ
ባኤ ለሚነሱት ሙታን ሁሉ የትንሣኤ
መጀመሪያ ነው ። የክርስቶስ ትንሣኤ
ሞትን ዳግመኛ የማያስከትል ከመሆ
ኑም ሌላ በኋለኛዪቱ ቀን ለሚነሡት
ሙታን መጀመሪያ ነው በብሉይ ኪዳ
ን ኤልያስ አንድ ምውት በጸጋ ቢያ
ስነሣ ነቢዩ ኤልሣዕም እንዲሁ ሁለ
ት ምውት ቢያስነሣ እንደገና ሞትን
ማስከተላቸው አልቀረም በሐዲስ ኪዳ
ንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አላዛርን
በሥልጣኑ ቢያስነሳው ዳግመኛ ሙቷ
ል ። ትንሣኤ ዘጉባኤንም ይጠብቃል ።
ጌታችን ሞትን ድል አድርጎ ተነሥ
ቷል በመዝሙር ፸፰ እግዚአብሔር ይነ
ሣል ጠላቶቹ አይሁድና አጋንንትም
ይበተናሉ ተብሎ በትንቢት ተነግሯ
ልና ።

ለምሳሌ ዮናስ ሦስት መዓልትና
ሦስት ሌሊት በከርሰ አንበሪ እንደተቀ
መጠ ፣ የሰው ልጅ ክርስቶስም ሦስት
መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃ
ብር አድሮ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ
ፍቱልኝ ሣይል በሥልጣኑ ተነሥቷል ።
አይሁድ ግን በሦስተኛው ቀን እነሣ
ለሁ ማለቱን ስለሰሙ መቃብሩን ታላቅ
ድንጋይ ገጥመው ፣ ጭፍሮችን ይዘው
አጽንተው ቆልፈው እስከ ሦስት ቀን
ቢያስጠብቁትም የባሕርይ አምላክ
ክርስቶስን በመቃብር ውስጥ አፍነው
ሊያስቀሩት አልቻሉም ። ትንሣኤውም
በአይሁድ ምቀኝነት ሊከሽፍ አልቻ
ለም ። በዮሐንስ ወንጌል ፲፩ ፣ ፳፭ ትን
ሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ብሏልና በእርሱ
ያመኑትን ሰዎች በፈቀደ ጊዜ ከሙታን
ለይቶ የሚአስነሣቸው የባሕርይ አምላክ
ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ሲነሣ የምቀ
ኞች ኃይል ምንም ሊገታው አልቻለም
ትንሣኤን አደርጋለሁ በትንሣኤም ኃይ
ሌን እገልጻለሁ ሲል ተናግሯልና ።

ኃይሉንም የገለጸባቸው መቃብ
ሩን በሚጠብቁት ሰዎች እንደሆነ ታው
ቋል የትንሣኤውን ብርሃን ከማየታቸው
የተነሣ በድንጋጤ ባሕር ሠጥመው
ነፍስ እንደተለየችው ሬሣ ሁነው ወድ
ቀው ተገኝተዋል ።

እንግዲህ ልናስተውለው የሚ
ገባ አንድ ነገር አለ ። ይህም ከሁሉ አስ
ቀድሞ ከአቤልና በዘጠኝ መቶ ሠላሣ
ዘመን ከሞተ አዳም ጀምሮ እስከ ኋለኛ
ይቱ ቀን የሚሞቱ ሰዎች ትንሣኤ ዘጉ
ባኤን ሲጠብቁ ይኖራሉ ። የጌታችን
ትንሣኤ ግን ትንሣኤ ዘጉባኤን አልጠ
በቀም ። ምክንያቱም ክርስቶስ በኩረ
ትንሣኤ ሙታን መሆኑ ተጽፏልና
ነው ። ሞትንም ድል አድርጐ በተነሣ
ጊዜ መላእክትና ቅዱሳት እንስት በመ
ካነ መቃብሩ ተገኝተው የዓይን ምስክር
ነት እንደሰጡ አራቱ ወንጌላውያን ሁሉ
በየምዕራፋቸው መስክረዋል ።

ከትንሣኤም የምንወስደው
ትምህርት የሚሞት ሥጋ ወደ ዘለዓለ
ማዊ ሕይወት ፣ መዋቲ ሰውነትም ወደ
ኢመዋቲነት የሚሸጋገር መሆን እንዳ
ለበት ነው ። ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ
አንደኛ መልእክቱ ም. ፲፭ ቁ. 34 ስለ
ዚህ እንዲህ በማለት ተናግሯል "መሬ
ታዊ አዳምን መምሰልን ገንዘብ እንዳ
ደረግን ፣ ሰማያዊ ክርስቶስን መምሰል
ንም ገንዘብ እናደርጋለንና ብሏል ። ክር
ስቶስን መምሰል ማለትም ከሞት በኋላ
በትንሣኤ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው
ሥጋም በነፍስ ፈቃድ ለዘለዓለም በሕያ
ውነት መኖር እንዳለበት ነው ።

ከዚህ ላይ ልንረዳው የሚገባን አንድ
ሰው በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ቀን ተወለደ በዚህ ዘመን ሞተ ተብሎ የዘመኑ ማነስ ወይም መብዛት ይነገርለታል ። ይሁን እንጂ የሰው ሕይወት እስከሞት ብቻ ተወስኖ የሚቀር ወይም የሚያልቅ አይደለም ከሞት በኋላ ብትንሣኤ ተወልዶ እንደገና አዲስ ሕይወትን ተጐናጽፎ ማርጀትና ማፍጀት ሳይኖርበት ከበሽታና ከችግርም ነፃ ሁኖ ይህንን ያህል ዘመን ኖረ ፡ ተብሎ ዘመን የማይቆጠርለትና የዘመኑ ፍጻሜ የሌለው ለዘለዓለም በሕይወት የሚኖር ሕያው ፍጡር መሆኑን ነው ።

ለዚህ ማስረጃ የሚሆነውም በማቴዎስ ወንጌል ም. ፳፭. ቁ ፵፮ ጻድቃን ወደማያልፍ ሕይወት ይሄዳሉ የሚለው ኃይለ ቃል ነው ። ይህ ዕድል የሚገጥመው ግን የሕይወት ትንሣኤን ለሚነሱ ብቻ ነው ። ትንሣኤ ዘለደይንን የሚነሱ ኃጥአን (ሰዎች) ግን በትንሣኤው አይጠቀሙበትም ቢነሱም እድል ፈንታቸው ጽዋዕ ተርታቸው ከዲያብሎስ ጋር ስለሆነ በማቴ. ፳፭. ፵፭ ኃጥአን ወደማያልፍ ስቃይ ይሄዳሉ ተብሏልና። የትንሣኤ ሙታንን ምሥጢር ልናውቀውና ልንረዳው የቻልነው መድኃኒታችን ክርስቶስ ከሁሉ አስቀድሞ የትንሣኤ መጀመሪያ ሆኖ ስለተገለጸ ነው ። ስለዚህም "የሥጋችንን መነሣት ያስተምረን ዘንድ ክርስቶስ ተነሣ" የሚል ጽሑፍ ተጽፏል ። በእሱ ትንሣኤም የእኛ ትንሣኤ ታወቀ ።

በዕለት ስቅለትና ከመስቀሉ ሥር ከአምስት መቶ በላይ የሚሆኑ ሙታን ቢነሱም ከ፵ ቀን እስከ ፱ ቀን በማይበልጥ ጊዜ እንደ ገና ሞትን አስከትለዋል ። እሱን ግን ኢይመውት እምዝ ደግመ ይለዋልና ዳግመኛ ሞት የለበትም ።

ከተነሣም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የሠጣቸው መመሪያ እርሱ ከሚሠራበት ከነበረው ልዩነት አልነበረውም የባሕርይ አባቱ አብ እኔን ላስተምር ፡ ልሰቀልና ልሞት እንደላከኝ እናንተንም እልካችኋለሁ ካለ በኋላ ሂዳችሁ ሰውን ሁሉ አስተምሩ ስታጠምቋቸውም በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብላችሁ አጥምቋቸው" ያዘዝኋችሁንም ሁሉ አስተምሯቸው እኔም እነሆ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከናንተ ጋር ነኝ ሲል የመጨረሻ የተስፋ ቃሉን በዚህ አጠቃልሏል ።

ይህ የተስፋ ቃል ለጊዜው አብረው ለነበሩትና ትምህርቱን ይሰሙ ለነበሩት ሐዋርያት ቢሠጥም በእነሱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም ። ያንጊዜ ለነበሩት ዛሬም ለአሉት እስከ ዓለም ፍጻሜም ለሚነሱት ሐዋርያት ሁሉ የተሠጠ ተስፋ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው ።

እንግዲህ ከእውነተኞች ሐዋርያትና መምህራን እንደማይለይና አድሮባቸውም እንደሚኖር ስለአስረዳን እኛም ወንጌልን ከማስተማርና ከወንጌል ጉባኤ መለየት አይኖርብንም ። ባለቤቱም የሚያዘንን ትእዛዝ አክብረን ብናስተምር ነው እንጅ በስም መምህራን በመባል ብቻ አይደለም ።

ስለዚህም የሚያስረዳን ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ የነበረው እስጢፋኖስ ወንጌልን በሚያስምርበት ጊዜ "ወረደ ተወለደ ፡ ተሰቀለ ፡ ሞተና ተነሣ" ብሎ በማስተማር ላይ ሣለ እግዚአብሔር ወልድ በባሕርይ አባቱ ቀኝ በኩል እንደተቀመጠ ሆኖ በማየቱ አካል ከሕልውና ተገልጾለት እግዚአብሔርን አመስግኗል ። ቅዱስ ጴጥሮስም ምሥጢረ ትንሣኤውን አምልቶ አስፍቶ ለሕዝቡ ቢነግራቸው ምን እናድርግ አሉት ። ድህነትን ከሻችሁ እመኑ ተጠመቁ አላቸው ። በአንዲት ቀን አምስት ሽህ ያህል ሰዎች አምነው ተጠመቁ እንግዲህ ቅዱስ ጴጥሮስ የጌታችንንሞትና ምሥጢረ ትንሣኤውን አምልቶ አስፋፍቶ ሲያስተምር በቀን እስከ አምስት ሽህ አስተምሮ በማጥመቁ ክርስቶስን በግብር መስሎታል ለማለት ይቻላል ።

እኛም ቢሆን እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ የክርስቶስን መሞትና መነሣት ለአመኑበት ሰዎች ሕይወት እንደሆነ አምልተን አስፍተን ቃለ ወንጌልን ከዳር እስከ ዳር ብናስተምር ፡ በተማርነውም ጸንተን ብንኖር ክርስቶስ በእኛ እንደሚኖርና ከእኛ እንደማይለይ በማያልፍ ዘለዓለማዊ ቃሉ አስተምሮናል ።

ዮሐንስ ፲፭ ቁ. ፬ "በትምህርቴ ጸንታችሁ በእኔም አምናችሁ ኑሩ እኔም በእናንተ አድሬባችሁ እኖራለሁ" ይላል፤ ከትንሣኤ ሙታን በኋላም ያለውን ተስፋ ሲገልጽልን "እኔ ከሄድኩ ፡ መንግሥተ ሰማያትንም ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ ሁለተኛ መጥቼ እኔ ወደ አለሁበት እወስዳችኋለሁ ፡ እናንተም እኔ ወደምኖርበት ትኖሩ ዘንድ" ሲል በማይታጠፍ ቃሉ ያለንን ተስፋ ገልጾልናል ።

እንግዲህ ከእርሱ ጋር የምንኖር ከሆነ ፡ ከእሱም የማንለይ መሆኑ ከተገለጠልን ፡ ከዚህ የበለጠ ሕይወት ከዚህ ሌላም ክብር ሊኖር አይችልም ። የሰማይ አባታችን እንደመሆኑ መጠን ልጅ የአባቱን ሀብት እንዲወርስ እኛንም በትሩፋተ ደሙ ዋጅቶ የመንግሥተ ሰማይ ወራሾች አድርጎናል ።

ስለዚህ በእርሱ ትንሣኤ የእኛን መነሣት ፡ በእርሱም ወደ ሰማይ መውጣት የእኛን ወደ ሰማይ መውጣት ልንገነዘበው ይገባል ። "ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ በማለት ራሱ ጌታችን ተናግሯልና"።

መ/ ኪዳነ ማርያም አየለ



# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## "ቅዱሳት አንስት"

" በጌታ ዘንድ በሴትና በወንድ መካከል ልዩነት የለም ሁለም አንድ ናቸው ይላል ገላትያ ም.፫ ቁ.፳፰" ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን የወንዶችም የሴቶችም የሁሉም ናት ። ሁሉም በኅብረት ያገለግሏታል ይገለገሉባታልም የምትደገፈውም በወንዱ ብቻ ሳይሆን በሴቷም ጭምር ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት/ጊዜ ብዙ ወንዶችና ሴቶች የእርሱን ትምህርት ለመከታተልና የሚሰጠውም መልስ ስለሚያረካቸው አብረውት ይከተሉት እንደነበር ያስረዳናል ።

በተለይም በሉቃስ ወንጌል ም.፰ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ሴቶች ይከተሉትና በገንዘባቸውም ያገለግሉት እንደነበር መጽሐፉ ያረጋግጣል ። ይህ ብቻ ሳይሆንም በጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን እንዳትፈርስ ፀንታ እንድትኖር ይጥሩ ከነበሩት መቶ ሃያ ቤተሰብ መካከልም ሠላሳ ስድስቱ" ቅዱሳት አንስት" እንደሚገኙበት እሙን ነው።

ይህች ፆታና ወገን የማይለይባት ቤተ ክርስቲያን የምትሰጠው ክብር እንደዚሁ የጋራ ሁኖ እናገኘዋለን ለዚህም ቅድስናን በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን ቅድስና ለወንዶች ስትሰጥ ለሴቶችም እንደዚሁ ትሰጣለች ማለትም ሁሉንም በእኩልነት በመመልከት ለወንዱ ቅድስና ስትሰጥ ለሴቷም" ቅድስት......" በማለት የቅድስናን መአርግ ትሰጣለች ።

ለወንዶቹ የመታሰቢያ ዕለት እንዳላቸው ሁሉ ለሴቶችም የመታሰቢያ ዕለት ተሰጥቷቸዋል ለዚህም ሳምራዊቷን ሴት የወሰድን እንደሆነ በግሪካውያን ዘንድ ታላቅ ቦታ አላት ትንሣኤ በዋለ በ፫ኛው ሣምንት የሳምራውያን ብርሃን ሣምንት በመባል ሳምንቱን ሙሉ የእርሷ መታሰቢያ ሳምንት እንዲሆን ተወስኖ ይከበራል ። የኛም ቤተ ክርስቲያን ለቅዱሳን ለሰማእታት ለጻድቃንም የመታሰቢያ እለት ሰጥታ እንደምታከብርላቸው ሁሉ ሴቶችም ምግባር ትሩፋት በፈጸሙበትና ገድል በታጋደሉበት እለት በማስታወስ የመታሰቢያ እለታቸው እንዲሆን ወስና ሰጥታቸዋለች ።

ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶች ያማልዳሉ ብላ እንደምታምንባቸው ሁሉ እንደዚሁም ቅዱሳት እናቶችም በምግባራቸው በትሩፋታቸው የበቁ ከሆኑ እንደሚያማልዱ ታምንባቸዋለች አማላጅነታቸውም እሙን ነው ።

ስለ ክርስትና እምነት መስፋፋትም የክርስቶስንስም የሚጠራ ሁሉ በሰይፍ ይታረድና በእሳትም ይቃጠል በነበረበት በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሰማዕትነት ያረፉ ብዙዎች እናቶች ናቸው ለዚህም ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለወንዶች ስማዕታት የተሰጠውን ክብር ለሴቶች ሰማእታትም ሰጥታቸዋለች ። በዚህም ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጠቅላላ የቅዱሳት ሴቶችን የመታሰቢያ እለት የዳግም ትንሣኤ ዋዜማ ቅዳሜ ታከብራለች ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ቅድስና ፡ መታሰቢያ ፡ አማላጅነት የተሰጣቸው በሕይታቸው ዘመን ባደረጉት አገልግሎት ነው ። ቅዱሳት አንስት ለክርስቶስ የሰጡት አገልግሎት ምንድን ነው? ወደሚለው ጥያቄ ብንሄድ ፡

፩/ አብረውት ነበሩ ፪/ በገንዘባቸው አገልግለውታል ፫/ ትንሣኤውን በመጀመሪያ በማየት ለሐዋርያት ነግረዋል ።

፬/ በመጀመሪያው መቶ ዓመት ቤተ ክርስቲያን በከባድ ችግር በነበረችበት ጊዜ ለክርስቲያኖች ብዙ አገልግሎት አድርገዋል መላ ሕይወታቸውንም አሳልፈው እስከ መስጠት ደርሰዋል ።

፭/ የሐዋርያነት መልእክታችንም ለማህበረ ቤተ ክርስቲያን አዳርሰዋል ።

፮/ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን በቤታቸው እንድትመሠረት አድርገዋል

፯/ ያላመኑትንም በማስተማር አሳምነዋል

፰/ ትንቢት በመናገር የመንፈስ ቅዱስ የተስፋ ትንቢት በእነርሱ ተፈጽሞአል

፱/ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ከተጀመረ በኋላም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸመውን ልዩ ልዩ አገልግሎት በማከናወን ሠርተዋል ።

ይህም የመጀመሪያዋ እምነት የተመሠረተችው በምድረ ይሁዳ እንደመሆንዋ መጠን አሪታዊ ሥርዓት ፈጽሞ አልጠፋም ነበር ኦ.ዘፀ.ም.፴፰ቁ.፰ እንደሚያመለክተው በአዲስ ኪዳንም ያንኑ አገልግሎት ይሠሩ ነበር ።

ከዚህም ሌላ ፩. በብህትውና ፪. በጸሎት ፫. በጾም ተወስነው ለሀገር ለወገን ለዓለም ሁሉ መላ ሕይወታቸውን ያሳለፉ ቅድሳት እናቶች ነበሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

ይህንንና ይህንን የመሳሰለውን በመ
ፈፀማቸው ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት የ
ሚለውን የቅድስና ስም ሰጥታቸዋለች
ስለዚህ እኛም ዛሬ የነዚህን ቅዱሳት
ሴቶች /አርአያ በመከተል መልካም ገ
ድል መጋደል አለብን ወንጌልን ማስተ
ማር ግዴታችን ነው የወንጌል ትምህር
ት ባደባባይ ብቻ አይደለም የሚሰጠው
በመጀመሪያ መሠረቱ የሚጣለው በቤ
ት ውስጥ ነው ።

እናቶች ለልጆቻቸው ፣ ለቤተሰባቸ
ው ሀልወተ እግዚአብሔርን ያስተምሩ
የእናቶች ትምህርት ዘመንና እድሜ የማ
ይሽረው ከአእምሮ ተቀርፆ የሚኖር ሐ
ውልት ነው ቅዱስ ጳውሎስም በሚያስ
ተምርበት ወቅት ለደቀ መዝሙሩ ለጢ
ሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ "በአንተ
ያለውን ግብዝነት የሌለበትን እምነት
ህን አስባለሁ ይህም እምነት ቀድሞ በ
ያትህ በሉይድ በእናትህም በኤውንቄ
ነበረባቸው በአንተም ደግሞ እንዳለ ተ
ረድቼአለሁ " ፪ኛ. ጢሞ .ም. ፩ ቁ.፭.
ሲል የጢሞቴዎስ እናቱና አያቱ ምን ያ
ህል እምነተ ጠንካራዎች እንደነበሩና
እርሱም የእነርሱን አርአያ ይዞ ማደጉን
ያስረዳል ።

አዎ ልጆቻችን ማስተዋል ከጀመሩ
በት ጊዜ አንስቶ ከክርስቶስ ሥራና ፍቅ
ር ጋር መተዋወቅ ይኖርባቸዋል በትም
ህርታቸውም እግዚአብሔር አባታቸው
መሆኑን ማወቅ አለባቸው እግዚአብሔ
ር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ አስቀድ
ሞ እርሱን ማወቅና ለእርሱ መታዘዝ የ
ሥራችንና የሃሳባችን ሁሉ መነሻና መ
ድረሻ ሊሆን ይገባዋል ይህንንም ሁሉ
በቤት ላሉት ማስተማር የእናቶች ግዴ
ታ ነው ።

# የሊቀ ጠበብት

ከገጽ ፱ የዞረ

ትርጓሜው እኔ ግን አገልግሎቴን ፈ
ጽሜ ጨርሻለሁ የማርፍበትም ጊዜ
ደርሷል መልካም ገድልን ተጋድያለሁ
ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠ
ብቄአለሁ ወደፊት ኵናኒ በጽድቅ ፈታ
ሂ በርትዕ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን የጽድ
ቅ አክሊል ያስረክበኛል የተባለው የጳ
ውሎስ ቃል በሊቀ ጠበብት መስፍን ኃ
ይለማርያም የተፈጸመ ስለሆነ በዚሁ ዕ
ለት እንዲጠቀስ አስፈልጓል ሆኖም አ
ዳም ሆይ! መሬት ነህና ወደ መሬት ት
መለሳለህ ባለው አምላካዊ ቃል መሠረ
ት በሞት ሥልጣን ተይዘው የካቲት ፴
ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በተወለዱ በ፹፰ ዘ
መናቸው ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸው
እንዲሁም የሥራ ጓደኞቻቸው ካህናት
ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩን መሪር ኀዘን
ተሰምቶናል ኃያሉ እግዚአብሔር ለቤ
ተሰቦቻቸው መጽናናትን እንዲሰጣቸ
ውና ነፍሳቸውንም ከወዳጆቹ ከአብር
ሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብ አጠገብ እን
ዲያኖርልን እንለምናለን ። አሜን ። ...
ከመንበረ ፀባዖት ቅ/ሥ/ካቴ/ጽ/ቤት

# ከደብረ ዘይት እስከ ሆሣዕና

በዚሁም በሁዳዴ ጾም ቤተ ክርስቲ
ያን የምትጾመው ጾም የጌታችን የአም
ላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾም እንደ
መሆኑ መጠን በዚሁ ወራት ጌታ በዚህ
ዓለም በሥጋ ተገልጦ ለሠራቸው የተ
አምራትና የትምህርት ተግባራት መታ
ሰቢያ በዓል በማድረግ ለእያንዳንዱ ሰ
ንበት ስም በመስጠት የምትዘምርበት
ንና የምትቀድስበትን ሁኔታ ለማብራ
ራት በአለፈው ጽሑፍ ከዘወረደ እስከ
መጻጉዕ በሚል ርዕስ የመጀመሪያዎቹን
የአራቱን ሰንበታት ስያሜና ይትበሃል
ከቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢርና ከጾ
መ ድጓው ባህል ጋር በማዛመድ ታሪካ
ቸውን በመጠኑ ገልጸናል ።

በዛሬው ጽሑፍ ደግሞ ከደብረ ዘይ
ት እስከ ሆሣዕና ያሉት ሰንበታት ስያ
ሜና ትርጉም ምን እንደሆነ ለማሳወ
ቅ እንሞክራለን ይኸውም ከመጻጉዕ በ
ኋላ ያለው አምስተኛው ሰንበት ደብረ
ዘይት ሲባል ስድስተኛው ሰንበት ገብር
ሄር ተብሎ ይጠራል ። ከእሱም ቀጥ
ሎ ያለው ሰባተኛው ሰንበት ኒቆዲሞስ
ይባላል ስምንተኛውም ሰንበት ሆሣዕና
የሚል ስም አለው። በዚህ ጽሑፍ የም
ንሰጠውም የእነዚህን ከዕኩል ጾም በኋ
ላ ያሉትን የአራቱን ሰንበታት ዝርዝር
ታሪክ ነው ።

፭ኛ ደብረዘይት

የጌታችን የመድኃኒታችን የፈጣሪያ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾም አማካይ ሰ
ንበት ወይም ዕኩል ጾም ላይ የሚውለ
ው እሑድና ሳምንቱ ደብረዘይት የተባ
ለበት ምክንያት ከዚሁ ሰንበት ዋዜማ
ጀምሮ የሚዘመረው ጾመ ድጓ"እንዘ
ይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት
ቀርቡ ኀቤሁ ኵሎሙ አርዳኢሁ በዕለተ
ሰንበት ወይቤልዎ ንግረነ በምንት ይከ
ውን ተአምሪሁ ለምጽአትከ ወለኀልሀቀ
ተ ዓለም ጌታችን በደብረ ዘይት ተቀም
ጦ ሳለ በዕለተ ሰንበት ደቀ መዛሙርቱ
ሁሉ ወደ እሱ ቀረቡና የመምጣትህ ም
ልክቱ የዓለምስ ማለፍ ምልክቱ በምን
ይሆናል? ንገረን አሉት ። " እንዘ ይነብ
ር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ወይቤ
ሎሙ ለአርዳኢሁ ዑቁኬ ኢያስሕቱክ
ሙ..... እምበለስ አእምሩ እምሳሌሁ
ከመ በጽሐ ጊዜሁ ለማዕረር.... ሰማይ
ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀለፍ
ጌታችን በደብረዘይት ተቀምጦ ሳለ ለ
ደቀ መዛሙርቱ እንዳያስቷችሁ ተጠን
ቀቁ ምጽአት እንደደረሰ ምሳሌውን/ም
ልክቱን ከበለስ እወቁ ፣ ሰማይ ከምድር
ጋር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም"አላ
ቸው" እያለ ጌታ በደብረ ዘይት ምሥ
ጢረ ምጽአቱን ማስተማሩን እየጠቃቀ
ሰና እያነሣሣ ስለሚዘምር ይህ ሰንበት
ለዚሁ ጌታችን አምላካችን ወልደ እግ
ዚአብሔር በደብረ ዘይት የምጽአቱንና
የዓለም ኀልፈትን ነገር ለማስተማሩና ከ
ሐሰተኞች ነቢያት እንዲጠበቁ ለማስ
ጠንቀቁ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠነው
የዚህም በዓል ታሪክ ዝርዝር ሁኔታው
በማቴዎስ ወንጌል ምዕ.፳፬ቁ.፩ እስከ
መጨረሻው በማርቆስ ወንጌል ምዕ.
፲፫.ቁ.፩ እስከ መጨረሻው በሉቃስ ወ
ንጌል ምዕ.፳፩ ቁ. ፭ እስከ መጨረሻው
ተጽፎ ይገኛል ደብረ ዘይት በኢየሩሳሌ
ም ምሥራቅ የሚገኝ ተራራ ነው ጌታ
በዚህ ዳግመኛ የመምጣቱን ትምህርት
እንዳስተማረ ሁሉ ያረገውም በዚያ ተራ
ራ ነው ።

፮ኛ ገብር ኄር

ስድስተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ገብር
ኄር የተባለበት ምክንያት በዚሁ ሰንበ
ት የሚዘመረው ጾመ ድጓ ከዋዜማው ጀ
ምሮ "ገብር ሄር ወገብር ምእመን ገብ
ር ዘአሥመሮ ለእግዚኡ ጌታውን ያስደ
ሰተው አገልጋይ ታማኝና ቸር አገልጋ
ይ ነው' ገብር ሄር ወገብር ምእመን ዘ
በውጉድ ምእመነ ኮንከ ዲበ ብዙኀ እ
ስይመከ በጥቂቱ የታመንህ ቸር አገል
ጋይ ሆይ በብዙ እሾምሃለሁ" ዘበምልክ
ናከ ሠናየገበርከ ብፁዕ አንተ ገብር ሄር
በሹመትህ በጎ የሠራህ ምእመን ዘይ
ረክቦ እግዚኡ በምግባረ ሠናይ ወይሠይ
ሞ ዲበ ኵሉ ንዋዩ በደግ ሥራ ጌታው
የሚያገኘውና በገንዘቡ ሁሉ ላይ የሚሾ
መው ቸርና የታመነ አገልጋይ ማነው ?
"ለአግብርት ግዕዛን ለመሃይምናን ሰ
ላም ዛቲ ዕለት ሰንበተ ክርስቲያን ይቺ
ዕለት የክርስቲያን ሰንበት ለአገልጋዮ
ች ነፃነት ለአማኞች ሰላም ናት ኩኑ እ
ንከ ከመ አግብርት ኄራን ወከመ አግ
ብርተ ክርስቶስ ምእመናን እለ ይጸንሑ
እግዚአሙ እስከ የአቱ እምከብከብ ዘ
በሰማያት ፦ እንግዲህ እንደ ቸሮች አገ
ልጋዮችና በሰማይ ባለው መንግሥተ
እግዚአብሔር እስከ ሚገቡ ድረስ ጌታ
ቸውን ደጅ እንደሚጠኑ እንደ ክርስቶ
ስ አገልጋዮች ሁኑ ፦
"ጹሙ ወጸልዩ ከመ አግብርት ተቀነዩ
ጹሙ ጸልዩ እንደ በጎ አገልጋዮች /ለእ
ግዚአብሔር/ ተገዙ እያለ ጌታችን መድ
ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የካህናትና
የምእመናንን የጽድቅ ሥራ በመልካም
አገልጋይ ሥራ የኀጥአንን የበደል ሥራ
በክፉ አገልጋይ ሥራ እያመሳሰለ በወ
ንጌል ያስተማረውን ትምህርት በአጠ
ቃላይ ስለጻድቃንና ኃጥአን በምሳሌ
የተናገረውን ቃለ ወንጌል እየጠቃቀሰ
ና እያነሣሣ ስለሚዘምር ሰንበቱ ገብር
ሄር ተብሎ ተጠርቷል ።

ስለዚህም ይህ ሰንበት የጻድቃን መ
ታሰቢያ ዕለት ነው ። በዚህ ዕለተ ሰንበ
ት መታሰቢያነት የተሰጠውን የገብ
ር ሄርን የምሳሌ ትምህርት የምናገኘ
ው ቀጥሎ በተጠቀሱት የወንጌል ክፍሎ
ች ነው /ማቴ ፳፭-፲፬-፴፮ ። ሉቃ ፲፱ ፣
፲፪-፳፯ ። ፲፮፣፲ ማቴ ፲፫፣፲፪ ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ምዕራፎ
ችና ቁጥሮች ብንመለከት ስለ ገብር
ኄር ምሳሌነትና ስለጻድቃን ዋጋ እንዲ
ሁም ስለ ኃጥአን ፍዳ የተጻፉትን የም
ሳሌ አነጋገሮች ለማግኘት እንችላለን ።

፯ኛ ኒቆዲሞስ

ሰባተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ኒቆ
ዲሞስ የተባለበት ምክንያት በዚሁ ሰን
በት የሚዘመረው ጾመ ድጓ ከዋዜማው
ጀምሮ "ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምፈሪሳ
ውያን ዘስሙ ኒቆዲሞስ መልአኮሙ ለ
አይሁድ ዘሖረ ኀቤሁ ቀዲሙ ሌሊተ ወ
ይቤሎ ለኢየሱስ ዕጓለ አንበሳ ስከብከ
ወኖምከ አንሥአኒ በትንሣኤከ ስሙ
ኒቆዲሞስ የሚባል የአይሁድ አለቃ የ
ሆነ ከፈሪሳውያን ወገን አንድ ሰው
ነበረ እሱ አስቀድሞ ሌሊት ሄዶ ኢየሱ
ስን /በመቃብር/ አንቀላፋህም በትንሣ
ኤህ አንሣኝ" ያለው ነው ኒቆዲሞስ ስ
ገደ መንፈቀ ሌሊት ለዘቀደሰ ለሰንበት
ሰንበትን ለአከበራት ጌታ ኒቆዲሞስ በ
መንፈቀ ሌሊት ስገደ ይቤሎ ኒቆዲሞስ
ለኢየሱስ ረቢ ነአምን ብከ ከመ እምኀ
በ አብ መጻእከ ከመ ትኩን መምህረ ኒቆ
ዲሞስ ኢየሱስን ረቢ አብ መም
ህር ሆነህ ከአብ ዘንድ እንደመጣህ እና
ምንብሃለን አለው" እያለ ኒቆዲሞስ
ሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ እየሔደ
ይሰግድ እንደነበረና ምሥጢረ ጥምቀ
ትን ከእሱ እንደተማረ እየጠቃቀሰና
እያነሣሣ ስለሚዘምር ይህ ሰንበት ለዚ
ሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኒቆዲሞ
ስን ለማስተማሩና ኒቆዲሞስ ከጌታ ለ
መማሩ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠ ነው፤
የዚህ በዓል ታሪክ ዝርዝር ሁኔታው በዮ
ሐንስ ወንጌል ም፫ቁ.፩.፳፩ ተጽፎ
ዋል ።

በዚህ ክፍለ ወንጌል ጌታችን ኢየሱ
ስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ምሥጢረ ጥም
ቀትን ብቻ ሳይሆን ርደቱን ስቅለቱን
አዳኝነቱን አስተምሮታል ። ኒቆዲሞስ
ከአርማትያሱ ከዮሴፍ ጋር ሁኖ ጌታን
የገነዘው ታላቅ ሰው ነው ። ስለዚህ ይህ
ሰንበት ከዚህ ጀምሮ የኒቆዲሞስ መ
ታሰቢያ እስከ ፫ ቀን ይከበራል ማለት
እስከ ማክሰኞ ድረስ የኒቆዲሞስ ቀኖች
ናቸው ።

፰ኛ ሆሣዕና

ስምንተኛው ሰንበት በኋላው ከአለ
ው ከረቡዕ ጀምሮ ሆሣዕና በመባል ይ
ታወቃል ። ይህን ስም ያገኘበት ምክን
ያት በዚሁ ሰንበትና በዋዜማዎቹ ዕለታ
ት የሚዘመረው ጾመ ድጓ "ሆሣዕና በ
አርያም የሆሣዕናን ቃል በየቦታው እየጠ
ቀሰና እያነሣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢ
የሱስ ክርስቶስ እየተመሰገነና እየተዘ
መረለት በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ኢ
የሩሳሌም የገባበትን ሁኔታ እየተረከ ስ
ለሚዘምር ይህ ሰንበት ለዚሁ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ በጌትነትና በክብር
በውዳሴና ቅዳሴ ሆሣዕና በአርያም እ
የተባለ በሽማግሌዎችና በሕፃናት አንደ
በት በድንጋዮች ልሳን ሳይቀር እየተመ
ሰገነ ኢየሩሳሌም በአህያ ተቀምጦ ለ
መግባቱ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠ
ነው ። የዚህ በዓል ታሪክ ዝርዝር ሁኔታ
ው ቀጥሎ ባሉት ምዕራፎችና ቁጥሮች
ተዘርዝሮ ይገኛል ።
/ማቴ.፳፩.፩-፲፯ ። ማር ፲፩፣-፩-፲ ። ሉቃ
፲፱፣፳፱-፴፰፣ዮሐ ፲፪፣፲፪-፲፰ ዘካ ፱፣፱።
፪ኛ/ ነገ ፱፣፲፫ ። መዝ ፩፻፲፰፣፳፭-፳፮
ኢሳ ፶፮፣፯ ። ኤር ፯፣፲፪ ።መዝ ፰፣፪ ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ምዕራፎ
ችና ቁጥሮች በጽሞና ብንመለከት ስለ
ሆሣዕና በትንቢት የተነገሩትንና በድር
ጊት የተፈጸሙትን መረዳት ይቻላል ።

ቀደም ባለው ጽሑፍ እንደተጠቀሰ
ው የሰንበታቱ ስያሜ በቂ የሆነ የቅድሳ
ት መጻሕፍት ታሪክ ድጋፍ ያለውን የጾ
መ ድጓውን ባህል የተከተለ መሆኑን
በማስታዎስ ጽሑፋችን በዚህ እናጠቃ
ልላለን ።

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ





www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግዕዝ= የግዕዝ ትምህርት

ትምህርተ ቃላት ወሰዋስው ዘግዕዝ መክሥት ፡በእንተ ትምህርት ዘዮም የዛሬው ትምህርታችን በተለይ በል ደትና በጥምቀት ሰሞን በሚነገሩት ቃ ላት የተመሠረተ ድብልቅ ዓረፍተ ነገር ይሆናል ።

ዓረፍተ ነገሮችንም ለመሥራት በመጀ መሪያ እነዚህን ቃላት እናጥና

## ቃላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጉል | በረት | ሰብሐ | አመሰገነ |
| ፀርቅ | ጨርቅ | ሰማያት | ሰማያት |
| አፅርቅት | ጨርቆች | ምድር | ምድር |
| ኩሉ | ሁሉ | ኖላዊ | እረኛ |
| ዮም | ዛሬ | ኖሎት | እረኞች |
| እግዚእ | ጌታ | በግዕ | በግ |
| ዓለም | ዓለም | አባግዕ | በጐች |
| ቤዛ | ቤዛ | ጠብሐ | አረደ |
| ፀንሰ | ፀነሰ-አረገዘ | ብዙኅ | ብዙ |
| ተፀንሰ | ተፀነሰ | ብዙኃን | ብዙዎች |
| ወለደ | ወለደ | እንቋዕ | እንኳ/እሰይ/ |
| ተወልደ | ተወለደ | በጽሐ | ደረሰ |
| ወልድ | ልጅ | አብጽሐ | አደረሰ |
| ወ | ና | ጠሊ | ፍየል |
| በ. | በ | አጣሊ | ፍየሎች |
| አምሐ | የእጅ መንሻ ስጦታ ለ | | ሉ-ይኩን ይገባል |

### ዓረፍተ ነገር

በጎል ሰከበ
በአፅርቅት ተጠብለለ
ዮም ተወልደ
እግዚእ ወመድኅን
ቤዛ ኩሉ ዓለም

### ሥምረት ፈቃድ

ሀ/ በኀላፊ ግሥ
በበረት ተኛ
በጨርቅ ተጠቀለለ
ዛሬ ተወለደ
ጌታና መድኅን
የዓለም ሁሉ ቤዛ

ለ/ በትንቢታዊና ምኞታዊ ግሥ
ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ብዙኃን አባግዕ ወአጣሊ ይጠብሑ በበ ዓለ ልደት-በልደት በዓል ብዙ በጐችና ፍየሎች ይታረዳሉ ኩሉሙ ሕዝብ ያበ ውዑ አምኃ ስብሐት ለእግዚአብሔር በዝ ዕለት በዚህ ዕለት ሰዎች ሁሉ ለእ ግዚአብሔር የምስጋና እጅ መንሻ ያቀ ርባሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማ ያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰ ብእ= ለእግዚአብሔር ምስጋና በሰማይ ይሁን ሰላም በምድር ለሰው በጐ ፈ ቃድ

እንቋዕ አብጽሐክሙ ለብርሃነ ልደቱ=
እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ
እንቋዕ አብጽሐከ ለብርሃነ ልደቱ =
እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሰህ

በዝ ይትፈጸመ ትምህርተ ግዕዝ ዘዮም ፡ እስከንትራከብ በዘይተሉ ትምህርትነ ሰላም ለከሙ ።

የዛሬው የግዕዝ ትምህርታችን ከዚህ ላይ ተፈጸመ በሚቀጥለው ትምህርት እስከንገናኝ ደኅና ሁኑ ።

# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየ ተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦ ችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቊ. 116616
የመልእክት ሣ. ቊ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org